


# ኢትዮጵያ

ታኅሣሥ / ጥር 2007 — 3ኛ ዓመት


**ዮሴፍ በሪ**
**የኢሕአወሊ/ኢሕአፓ አባል**
**በጀግንነት የታገለና በቀይሽብር**
**በደርግ ነፍስ ገዳዮች የተገደለ**


**ርእስ አንቀጽ ገፅ 2**
በነገሞራዉ ኪነ ጥበባዊ
ትልም፤ ምኔም ለሕዝብና
ለሀገር በጎዉን እናልም /

//

**ገፅ 3**

**ጋሼ ኃይሉ ገሞራው**
**አልሞተም !**

**ምን ይሰማ....... አገር**

//

**ዜናዎች ገፅ 4**

//

**ዴሞክራሲያ ገፅ 5**

//

**ትናንትና ገፅ 9**


## ሞቷል አትበሉ /

(በህያዉ ቃል )

አትበሉት “ ወደቀ” አፈር በላዉ በጨዉ
ቢገድሉት ቢገድሉት ያልጨረሱትን ሰዉ፤
“ ተከደኑ” አትበሉ “ ዓለምን ሰለቹ”
ግፍ መከራችንን ቀድመዉ ያዩ ዐይኖቹ
ከእጆቹ አሻራ -ከጣቶቹ ብዕር
በጠብታዉ ቀለም -በቋንቋዉ አቃቂር
በቦምበኛ ለዛ - በዉብ ቃላት ቅምር
ኃይሉ ሠርፆ እያለ ደረቶች ሰንጥቆ
እንደ መልከ ማርያም በድሆች ልብ ሠርጎ
በገሞራዉ ንዳድ፤
ሊኖር ሞትን ገድሎ -ዝንታ’ለም አርጎ ፤
አትበሉት ሞቷል፤
ቀድሞም እንዳይሞት ነዉ ምግባር አኗኗሩ
ባለቅኔዉ ብሁት፤
ቢራብ ቢጠማላት ቢሰደድ ላገሩ/
ለ’ማማ ኢትዮጵያ - ለሚወ’ዳት ምድር
ወገን ላለዉ ህዝቡ ለዕትብት ዘሩ ቁጥር
ሺህ አላሚ ልቡ
ሩቅ ሲያስብ ፤ ሩቅ ሲመኝ - ባይሆን ቅርብ ሲያድር፤
በዕድሜዉ መደምደሚያ ትንፋሹ ሲለየን
በረከት አዝናቢ ቃል ድምጹ ሲርቀን
እሰጥ ያ አይደለም ባለቅኔ ሞቱ
በአዳም ግብር ዕዳ ህቅታዉ ማብቃቱ
በቁም ሳለ’ንጂ ነዉ የገጣሚዉ ሞቱ
“ ባለቅኔ” ዕልፈቱ
መከራና ስቃይ ችግር ቀዬዉ ሞልቶ
ግፍ ባገር ሲታወጅ ዕንባ ሲጎርፍ ሞልቶ
ተረጋጩን ረስቶ
ከ’ዉነት ተካክዶ
ከ’ምነት መስመር ወጥቶ
ከረጋጩ ማዕድ ለቆረጠዉ ጮማ
ለተጋተዉ ኮኛክ
አደግድጎ ቆሞ ዉዳሴ ሲያሰማ ፤
ሻኛዉን ሊያሳብጥ እንደ ኮርማ ሰንጋ
ራሱን ሊደባልቅ ከዘረኞች መንጋ
ቃል ሲደርት በምጥ ሌሊቱን ‘ሚያነጋ
ጨዉ እንደለመደ ፤ የቆለኛ ጥጃ ከቶ ሳያሰልስ
ደም ያጨቀየዉን
የአንባገነኖች እጅ ጎንበስ ብሎ ‘ሚልስ፤
ላኩኝ ልላክ የሚል በተፈጥሮው እኩይ

በአቋም የሻገተ ፍልስምናዉ ሽንጋይ
ያ ነዉ የቁም ሙቱ
ገዥዎችን ከላይ ዐመጽን ገላጋይ
በሸበቶ ዕድሜዉ ሥር ዓትን አገልጋይ፤
እናም ፤
ከትዉልድ ተመዝዞ ከዘመን ተልቆ
ከኢትዮጵያ ጠላቶች በቁሙ ተናንቆ
ተገርፎ ተሰድዶ - በሥቃይ ተሳልቆ
እስኪደክም ኃይሉ
ሞቱን በቁም ገድሎ ኃይል የሆነን ሰዉ
አትበሉት “ወደቀ” አፈር በላዉ በጨዉ ፤

ለኃይሉ ገሞራዉ መታሰቢያ -በፍቅር
ታህሳስ ፪፻፯ ዓ.ም

# ልዩ እትም



የታላቁ ኢትዮጵያዊ የስነፅሑፍና የፍልስፍና
ሰው የኃይሉ ገብረዮሐንስ (ገሞራው)
(እ. ኤ. አ. 1935 – 2014)

**መከረኛዋ እማማ ኢትዮጵያ**
“ቸንክሮ የያዘሽ ካስማዉና አዉታሩ
ዓይነቱ ብዙ ነዉ ባድባሩ ባዉጋሩ
ከቶ እንዴት እናርጊሽ ልንፈታሽ ከሥሩ”

ገሞራዉ



**የኢትዮጵያ ጋዜጣን**
**በተለያዩ ድረ ገጾች**

**EPRP.COM**
**ASSIMBA.ORG**
**DEBTERAW.COM**
**ETHIOLION.COM**
**ወዘተ.**
- **FACE BOOK (ethiopianewspape**

# ኢትዮጵያ

**በኢሕአፓ የዲሲና አካባቢዉ ደጋፊ አካል**
**የሚዘጋጅ ወርሃዊ ጋዜጣ**

5309 Georgia Ave. NW 2nd floor Washington DC. 20011
ስ/ቁ፡ 202 291 4217
ኢሜል፡ dc..region.eprp@gmail.com

## ርዕሰ አንቀጽ

### በነገሞራዉ ኪነ ጥበባዊ ትልም፤
### ምኔም ለሕዝብና ለሀገር በጎዉን እናልም /

የየካቲት ፩፱፻፷፮ቱ ሕዝባዊ አብዮት በተወሳ ቁጥር የኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴም አብሮ መወሳቱ የግድ ነዉ ። ለዚህም መንስዔዉ ሁለቱ ክስተቶች በታሪካችን የሂደት መስመር ላይ ተከታታይ ሆነዉ የሚነጥቡ ከመሆናቸዉ የዘለለ ነዉ ። የባላባታዊዉን ሥርዓት አስከፊነትና ዉስጣዊ ቅራኔዎቹን ይፋ አዉጥቶ ከመዘክዘክና የዘዉዳዊዉን አገዛዝ ገመና ከማጋለጥ አንስቶ የሕዝቡን ብሶትና ቁጣ እንዲሁም ጥያቄዎቹን በመፈክር ደረጃ ቀምሮ እስከማስተጋባት ድረስ ያሉትን ተግባራት ደራርቦ በማከናወን የሀገራችን ተማሪዎች የተወጡት ድርሻና በህይወትም የከፈሉትን ዋጋ የሚዘክር ። በዚህ ረገድ ፤ ለአብዮቱ ጅማሮ እጅግ ወሳኝ የነበረዉን ማኅበራዊ ንቃተ ኅሊና በማጎልመስ ደረጃ ፤ የተማሪዉንና ከትምህርት ቤቶች ቅጽር ዉጭ የነበረዉን ኅብረተሰብ አስተሳሰብ ለመቀየር በተደረገዉ ጊዜ የፈጀ ጥረት ዉስጥ ኪነ -ጥበብ (በተለይም በሥነ ጽሁፉ ዘርፍ ) እና በዘመኑ ተማሪዎች የነበሩት ከያንያን የተወጡት ድርሻ ግዙፍ መሆኑን ታሪክ ዘግቦታል ።

በዚህ ወቅት ካፈራናቸዉ ሕዝባዊ የኪነጥበብ ጀግኖች መሃከል ስመጥሮቹ ጸገየ ወይን ገብረመድኅን (ጸጋዬ ደብተራዉ) እና ኃይሉ ገብረዮሃንስ (ገሞራዉ) ይገኙበታል ። ጭቆናና ረገጣ የሰፈነበት ሥርዓት ያለ ሕዝባዊ ዐመጽ እንደማይናድ ፤ ፍትህ ፤ እኩልነትና የተሟላ ነጻነት የሰፈነበት ኅብረተሰብም ያለትግል እንደማይገነባ ገና ከጠዋቱ የተገነዘቡት እነዚሁ ገናና ሕዝባዊ ባለቅኔዎች በሀገራችን ዉስጥ የተፈራረቁትን ግፈኛ አገዛዞች በተባ ብዕር በጽናት ተዋግተዋል ። የከፈሉት መስዋዕትም ከፍተኛ ነዉ ። ለዝናና ለንዋይ ሳይሳሱ ፤ ለእዉነትና ለሕዝብ ሲባል በሚደረግ ትግል ዉስጥ የሚያጋጥመዉን ፤ ከእስራት እስከ ስደትና ሞት ድረስ ያለዉን እንግልትና መከራም በጸጋ ተቀብለዉ በክብር አልፈዋል ።

በዘመን ንጽጽር ያለንበት ወቅት ሀገራችን ኢትዮጵያ የምትገኝበትን እጅግ አሳሳቢ ሁኔታና ሕዝቧም የተሸከመዉን የግፍ ቀንበር ክብደት ስናስተዉል፤ ከያንያን ሁሉ በደብተራዉና በገሞራዉ ፈለግ መከፈል የሚገባቸዉ ድርሻ የላቀ መሆኑን በአንክሮ እንገነዘባለን ። በበርካታ ትዉልዶች ጥረት የተገነባዉን ኢትዮጵያዊነት ለመናድ ሌት ተቀን የሚባትሉትን ዘረኞች ሤራ ለማምከን ፤ ዜጎቿ በእኩልነትና በነጻነት ዴሞክራስያዊ ሕይወትን የሚቋደሱባትን ሀገር ለመፍጠር በሚደረገዉ ትንቅንቅ ዉስጥ ወያኔያዊዉን አምባገነናዊ አገዛዝ እንቅልፍ የሚነሱ አያሌ ሕዝባዊ የብዕር ጀግኖች ሊፈጠሩ ይገባል ።

ሕዝባዊዉ ዴሞክራሲያዊ ትግል ያቸንፋል/
በነጻነቷ ኮርታ፤ ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር/

### የሀይሉ /ገሞራውን አስከሬን ወደ ሀገር ለመላክ የተሯሯጡት ሰዎች እውን የገሞራውን ኑዛዜ በተመረኮዘ ነው?

### እውነታ!

**ከ ዘነበ በቀለ**

”በዚህ ቀዳማዊ ደብዳቤዬ ላይ ብዙህን ቁምነገሮችን ለማስፈር እምብዛም አያመቸኝም ሊመቸኝ ካልቻለበት ወይም ከማይችልበት ምክንያቶች ውስጥ አይነተኛውና ተቀዳሚው ስለርስዎ ስለቀማኛው ማንነት በዝርዝር ለማወቅ ባለመቻሌ ነው። ስለቤተሰብዎ መሰረት ስለ ሶሻል ዕርከናዊ ደረጃዎ ስለትምህርት ጣራዎ ስለስራ ክፍልዎ ስለ ኑሮ ባህርይዎ በዝርዝር ባውቅ ኖሮ በሰፊው አሟልቼ እጅግ በሚያመረቃ አቀራረብ በፃፍኩልዎ ነበር። የእርስዎን ገበናዊ ራዕይ በመላ ምት ጅምላዊ ትኩረት ላይ ግን አንድ ነጥብ ፍንትው ብሎ በግልጽና በጉልህ ታይቶኛል። የሰውን መብታዊ ድንበር በመጣስ የህግን ሉዓላዊ ህንፃ በመናድ የነፃነትን የሰዎች ፀጋ በማርከስ ከግልዎ ሀብትና ንብረት ውጭ በጊዜያዊ ትምክህትና በማን አለብኝ ዕብሪታዊ ውጥረት የሌላ ሰው ዐፅመ ርስት መዝረፍዎ ነው። ይህ ድርጊትዎ ጥሩ ማጋለጫ ስለሚሆን 'ቢንጎ' ብያለሁ።" ይላል ገሞራው!

የቦታዉን የባለቤትነት መብት ለተጋፉ ሰዎች ማለትም ለወያኔ በግልፅ በፃፈው ጦማር ግርጌ በአራተኛው ገፅ ላይ 'መከርቸሚያ' በሚል ርዕስ ያሰፈረውን ግጥም መንጭቀው አውጥተው ኑዛዜው ነው ያሉን ሰዎች ከያቅጣጫው በሚደረግላቸው ትብብር ሲደናበሩ መመልከቱ አስቂኝ ነው።

**መከርቸሚያ!**

ባያውቁት ነው እንጂ የኔን ቋሚ ንግርት፣
በተወለድኩበት ነው የምቀበርበት
ሌላ ቦታ ሳይሆን በትውልዴ መሬት።

አስቀድሞም ቢሆን እትብቴ ተቀብሯል
ቀሪውም አካሌ በእርግጥ በክብር ያርፋል።
ሲንከራተት ኖሮ አካሌ የትም ምድር
በስተመጨረሻ የሚያርፍበት አፈር
ከተወለድኩበት ነው በክብር የሚቀበር።

በመቃብሬም ላይ በስተራስጌው በኩል
እኔም እንደርስዎ ህያው ነበርኩ የሚል
በትልቁ ቋጥኝ ላይ ተቀርፆ ይፃፋል
ይኸ ሁሉ ንግርት ከወዲሁ ታውቋል
ከዚያ ርስት ለመንቀል ታዲያ እንዴት ይቻላል?

በማለት ይገልጻል።

ገሞራው! እትብቱ በተቀበረበት ነው አስከሬኔ የሚያርፈው ሲል የተባረከ የተቀደሰ ብሎ በፅሁፉ ውስጥ ባሰፈረው ሃሳብ ተመርኩዞ መቃብሩ በአባቱ ቅጥር ግቢ ውስጥ እንዲሆን ምኞቱን ከመግለፅ ውጭ ሌላ አላለም። ነገሩን አወላግደው ለማቅረብ የፈለጉ ግለሰቦች ቪኦኤን ጨምሮ ግጥሙን እንደኑዛዜው በማስመሰል በንባብ ሲያቀርበው ትንሽ እንኳ የማጣራት እርምጃ ልውሰድ አለማለቱ ትዝብት ውስጥ የሚጥለው ነው። ወደ አስራ ስድስት ገፆች የያዘው የገሞራው ፅሁፍ የተፃፈው በ1999 እንደ ፈረንጆች አቆጣጠር ነው።

**'' የቅዱሳንን ዐፅመ ርስት ርኩሳን አይወስዱትም''**
**የማስጠንቀቂያ ጦማር ቁ. አንድ**
**ገሞራው ዘስዊድን**

በሚል ርዕስ የፃፈው ጦማር ሁኔታውን በግልፅ ያብራራል። በአጠቃላይ ፅሁፉም ሆነ ግጥሙ የሚያተኩረው በተቀማው የአባቱ ቤትና መሬት ላይ እንጂ ስለ አስከሬኑ ኑዛዜ አልነበረም።
"ላለፈው ምዕት ዓመት በሰብአዊነት አገልግሎት ላይ የቆየ ክቡር መካን በመሆኑም አንድ ትልቅ የመታሰቢያ ህውልት ታንፆበት ት/ቤት፣ መፃህፍት ቤት፣ የሆነ የታሪክ ተቋም ( Historical Institute) ለዘለቄታው ህያው ሆኖ መኖር እንዳለበት ለሰው ክብር የሚያስቡ ኢትዮጵያውያን ሁሉ የሚያምኑበት ሀቅ ነው።'' ሲል ምኞቱን ያሰፍራል። በተጨማሪም እንዲህ ይላል!

''አሁን ይህ ቦታ በዳረጎትነት ተሰጠኝ ብሎ የሚጨፍረውና ጮቤ የሚረግጠው ሰው በቀጣይ የፍትህ ወቅት የደም እንባ ከሚያለቅስ ዛሬውኑ አስረክቦ ዞር ቢል ይመረጣል። በዚህም ፍትሀዊ ድርጊቱ ከበስተሁዋላው ፀፀት ሊድን ይችላልና!! ብሎ በማያሻማ መልኩ ያስጠነቅቃል። በመቀጠልም ' አንድ ሀሙስ ዕድሜ የቀረው ወያኔ / ኢህአዴግ እየተደናበረች የምትሰራውን በደል ፍዳ ስቃይና መከራ በቆየ ልምዴ መሰረት ግጥምም ሆነ መጣጥፍ እያዘጋጀሁ የምጠዘጥዝበትን ለአቤቱታ መፃፊያ እንዳደርገው ጊዜ ስለወሰደብኝ እጅግ አዝናለሁ።' በማለት ተከታዩን ጦማር 3 ለማቅረብ ቃል ገብቶ ይሰናበታል።


በዚህ ፅሁፍ ውስጥ የት ቦታ አገሬ ወስዳችሁ ቅበሩኝ እንዳለ ግልፅ አይደለም። የሚያሳዝነው አሟሟቱ በውል ሳይታወቅ፣ ንብረቱ በህግ ሳይከበር በወንድሞቹ ልጆች አሸቃባጭነትና በአንዳንዶች ቸፍቸፍታ ገሞራው ባልፈቀደው ሁኔታ እንዲቀበር መሆኑ ያሳዝናል። ሆኖም ግን ታሪክና ትውልድ ሲያስታውሱት እንደሚኖሩም ጥርጥር የለውም።
ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!!!

## ጋሼ ኃይሉ ገሞራው አልሞተም !

***ሀማ ቱማ***

እውነቱን ለመናገር ታላቁን የኪነት ሰው ጋሼ ብዬው አላውቅም። ኃይሉን ኃይሉ ወይም ገሞራው ነበር ብዬ የምጠራው።የነበረኝ አክብሮት ግን ቅንጣትም ሳይቀንስ። ገሞራው ያኔ በዚያ ጊዜ ለእኛ ወጣቶቹ ዕንቁ አርአያችን ነበር። ተራማጅ የኢትዮጵያ ተማሪዎች አንቀሳቃሶች፤ የመሬት ለአራሹ ሰልፍ አቀነባባሪዎች ተብለው ከዩኒቨርስቲ ከተባበሩት ዘጠኞች አንዱ ነበር። ዝነኛው ነበር። በ1959 ዓ. ም. ደግሞ ''በረከተ መርገም''ን ገጥሞ ዳግም ከስርዓቱ ሲጋጭና ችግር ሲገጥመው ገዘፈ። ሙሉውን ያንብቡ . . .

"ሲነድ ሲቃጠል የሚስቅ እሳት ነው … ያሰብከው ዓላማ አልሆን ብሎ ሲከሽፍ ሁናቴው ሲጠጥር ጠጣሩ እንዲላላ የላላውን ወጥር"
ያለው ዛሬም ትምህርት አዘል ሆኖ ትግላችንን አጃቢ ነው።
ኃይሉን ላውቀው የቻልኩት በወዳጄና ጓደኛው በጸጋዬ ገብረ መድህን





ደብተራው አማካይነት ነው። ሁለቱም የቤተክርስቲያንን ትምህርት ጠንቅቀው የተማሩና ቀዳሽም፤ ባለቅኔም ስለነበሩ (የገሞራው አባት ካልረሳሁ የእስጢፋኖስ ቤተክርስቲያን መሪ ጌታ ነበሩ) ጓደኝነታቸው ጥልቅና ለረጅም ዓመታትም የዘለቀ ነበር። ሁለቱም ቀልድና ጨዋታን የሚወዱና የማይከብዱም ነበሩ። ትሁቶችና የማይኩራሩ፣ እምነታቸው ህይወታቸውን የቃኘ ምርጥ ግለሰቦች ነበሩ። ገሞራው በጻፈው ግጥምና በራሱ አነሳሽነት ስርዓቱን ተቃዋሚ እርምጃዎች በመውሰድ ተንቀሳቃሽ ነበርና በየጊዜው እየተያዘ ወፌ ኢላላና ሌሎችንም ስየሎች እየተቀበለ ግን አልበገር ብሎ የቆመ በመሆኑ ለሁላችንም አርአያ ሆኖ ለትግል ያለንን ስሜት አጠናክሮልናል። ገሞራው ደፋር፤ ኢትዮጵያን ወዳድ፤ አሰባሳቢና ምሳሌ ነበር ብል ስህተት አይደለም። የደረሰበት ስየል፣

ዛሬ ዕድሜ ለደርግና ወያኔ ተራ መስሎ ቢታይም ለያኔ (ለነገሩ ዛሬም) ግን አሰቃቂ ነበር ። ገሞራው ግን በዚህ አልተረታም። ወደ ቻይና ለትምህርት ሄዶም አስከፊ ዘረኝነትንና መከራን ቢቀበልም ይህንንም በተለመደው ተቃውሞ እያጋለጠ ችሎ ሊያልፈው ችሏል። ቻይና የወለዳቸውን ሁለት ልጆች ይዞ እንዳይወጣ የቻይና መንግሥት ኣግዶት ሰፊ ትግልም ኣካሂዶ ነበር። የቻይና ቋንቋ ፈሊጣዊ አነጋገሮችን ወደ እንግሊዥኛ ተርጉሞም ሰፊ መዝገበ ቃላት ሊጽፍና ሊያሳትም ችሏል፡፡ ወደ ኖርዌይና ስዊድን ተሰዶ ሳለም የደረሰበት ግፍ -- እነዚህ ሀገሮች የተገንጣዮችና ጠባቦች ጥብቅ ወዳጆች ነበሩና -- በቀላሉ የሚገመት አይደለም። የሚወደው ወንድሙን ዶክተር እጓለንም ወደኬንያ ሄዶ እንኳ ሊያየው ሳይችል ዶክተር እጓለ አርፏል። መንግስታትና ተገንጣዮች ባላቸው ወዳጅነት የተነሳና በእነዚህም ሀገሮች ጠባቦችና ገንጣዮች ድጋፍ ያላቸው ነበሩና ገሞራው መብቱ ተረግጦ ቢሰቃይም ግን አንዴም ቢሆን ሳይንበረከክና ቀቢጸ ተስፋ ሳያደቀው ጠንክሮ በመታገል ወገንና ሀገርን ያኮራ ጀግና ነው።

ለእኔ በግሌ ደግሞ ታላቅና አዋቂ ብዬ የማከብረው ነበርና፣ ግጥም የምችል መስሎኝ ''ግጥም የት አውቄ'' የምትል ስብስብ ልኬ አስተያየት ስጠኝ ስለው፣ የሽፋኑንም ሰዕል አስርቶ፣ በራሱ ኪሳራ አሳትሞልኝ፣ በርታ ቀጥልበት በሚል የግጥም ሙከራዬን እንድቀጥል ያበረታታኝ ነው። ገሞራው ወገኖቹን የሚታደግ ሁሉን ማለት ይቻላል አፍቃሪ የነበር ሲሆን በኢትዮጵያ ጠላቶች ላይ ግን ጥላቻውና ተቅውሞው መቸም ያላሰለሰ ነበር። ወያኔና ሻዕቢያን ወሾ/ውሾ ብሎ ያጋለጠው ገሞራው በእነሱም ሆነ በሚደግፏቸው የደረሰበት ጥቃት ቀላል አልነበረም። ገሞራው ግን ከቁም ነገር አልቆጠራቸውም። ዕይታው ሰፊና ጥልቅ ነበርና ውሎ አድሮ መውደቃቸውን የሚያምን ነበርና በቀቢጸ ተስፋ አልተጠቃም። በአካሉ ስቃይና መከራ ቢደርስበትም በመንፈሱ ግን ጠንካራና ባለብሩህ ተስፋ ሆኖ ምድራዊ ህይወቱን አሳልፏል። ህያውነቱ ግን ቀጣይ ነው።

''ሲነድ ሲቃጠል የሚስቅ እሳት ነው!'' ያለው ኃይሉ በመከራው እየሳቀ፤ ጠላቶቹ ላይ እየተሳለቀ ኖሯል፤ ታግሏል፤ ወገንን ቀስቅሷል። ያደረበት ህመም ሲጸናበት፤ የወያኔ ደጋፊው ጥቃት ሲበዛበት፤ የሚያየው ክህደት ሲያበሳጨው ወደ መኖሪያው ስዊድን ሄጄ አግኝቸው ልንወያይ መቻላችን ዛሬ መልካም ትዝታ ሆኖልኛል። የተለመደው ሳቁና አነጋጋሩ እንዳለ ሆኖ ስለ ጸጋዬምና ሊሎች ጉዳዮች ስንጨዋዎት እኔን የሚያበረታታ እንጂ በቀቢዖ ተስፋ የተጠቃ ወዳጅ አላገኘሁም። ግጥም መጻፍ ቢያቆምም የፃፋቸው ጠባብ ቤቱን አጨናንቀውት ነበር። በርቱ ታገሉ እንጂ በቃችሁን አላሰማኝም። ወዳጁ ደብተራው ይሙት ይኑር አለማወቁ በጣም ይከነክነው ነበርና ''ጠላታችን ወያኔ ዛሬም ቢሆን ነገ ዋጋውን ይከፍላል!'' ይለኝ ነበር። ዛሬ ጋሼ ኃይሉ በደረሰበት መከራና በሽታ ህይወቱ ቢያልፍም ሁሌም ከእኛ ጋር ነው። ቅርሱ ኢትዮጵያዊነት፤ ጽናት፤ ቃል ኪዳንን ማክበርና ወገንን ማፍቀር ነው። የጽናት እና የፍቅር ብቻ ሳይሆን የደግነትም አባት ነው። ገሞራው በማረፉ ደስታ የተሞሉት ሁሉ የኢትዮጵያ ጠላቶች ናቸው። ታላቁ ሰው ገሞራው አረፈ ብሎ መዘገቡ ሁሉ የተሳናቸው ሁሉም የኢትዮጵያ ጠላቶች ናቸውና አቋማቸውን አንርሳ። የሀገራችን ታላቅ የጥበብ አባት ሲያርፍ መዘገቡ ተራራ ከሆነባቸው፣ እንዴት ነው ለኢትዮጵያ ያላቸው ወገንተኛነት የሚለካው? ''ጠላትማ አንድ ጊዜ ጠላት ነው/ አስቀድሞ መግደል አሾክሿኪውን ነው!'' የሚለውን አባታዊ አባባል ማስታውሱ በጭቃ እሾሆች የሚደርስብንን ጥቃት ለመከላከል ይረዳናል።

ኃይሉ በቅርሱ ሕያው ነው!
ሞት ጀግናን አያቸነፍም !!
ትዝታህና ምሳሌህ ትግላችንን ያበረታታል ጋሼ ገሞራው !!

## ምን ይሰማ……አገር?



**"ኢትዮጵያ በዓለማቀፉ የቴሌኮሙኒኬሽን ህብረት የዕድገት አመላካች ሠንጠረዥ ከ፻፷፮ (አንድመቶ ስድሳ ስድስት) አገሮች ፻፷፪ኛ (አንድ መቶ ስድሳ ሁለተኛ) ደረጃን አገኘች ።"**

*(አይ ቲ ዩን በመጥቀስ ድሬ ትዩብ በ ፲፩ /፳፬ / ፪፻፲፬ እንዳሰፈረዉ )*

- **እነዚህ ደረጃ መዳቢዎች ፤ የ ፲፩ ከ፻ (አሥራ አንድ ከመቶ) ዓመታዊ ዕድገታችንን አልሰምተዉም እንዴ ?/**

//

**" የኢትዮጵያ መንግሥት ለዓለም ገበያ የሚያቀርበዉ "የሰቨሪን ቦንድ " መጠን ዛሬ ይፋ እንደሚሆን ተመለከተ ።"**

*(አፍቃሬ ወያኔዉ ሪፖርተር ጋዜጣ በ ፲፩ / ፳፮ /፪፻፲፬ ያሰፈረዉ ዜና )*

- **"የበላችዉ ያገሳታል ፤ በላይ በላዩ ያጎርሳታል ፤" ማለት አሁን ነዉ ። ሪፖርተሮች ፤ ለመሆኑ ኢትዮጵያ መንግሥት አላት እንዴ ??**

//

**" ተስፋዬ ተስፋ ሲቆርጥ ......."**

*(ተስፋዬ ገ/መድህን በኢትዮ ሚድያ ድረ ገጽ ያስነበቡት መጣጥፍ ንዑስ ርዕስ )*

- **አሁንም ስለተሸጠዉ ሰይጣን እያወራን ነዉ ?/ ተስፋ የቆረጠዉ ተስፋዬ ነዉ ፤ ወይስ ስለርሱ አዉሪዎቹ ?/ ቀድሞ ነገር ፤ ማን ያን ያህል ካበዉ ?/**

//

**"ኢሕአዴግ ለመግደልና ለማሰር ቆራጥ ነዉ ፤ እኛም ለምንወዳት ሀገራችን ያለችንን አንድ ህይወት ለመስጠት ቆራጥ ነን ፤"**

*(የሰማያዊ ፓርቲዉ ኢ/ር ይልቃል ጌትነት ባስደመጡት ንግግር የተጠቀሙበት ገለጻ ፤)*

- **ኢሕአዴግ" የሚለዉን ካባ አዉልቀን "ወያኔ" በሚለዉ ተገቢ መጠርያ ከመተካት በቀር ለአባባልዎ ሳንክ አይወጣለትም ። ከልብ ካለቀሱ ዕንባ አይገድም ።**

//

**" ዓለማቀፉ የወንጀል ችሎት ( አይ ሲ ሲ ) በኬንያዉ ፕሬዚዳንት ኡሁሩ ኬንያታ ላይ መሥርቶት የነበረዉን ክስ አነሳ ።"**

*( ቢቢሲ በ ፲፪ / ፭ / ፪፻፲፬ የዘገበበት ርዕሰ ዜና ፤)*

- **በነስብሃት ነጋ ሠፈር ሲደለቅ ከርሟላ ። ግን ግን ዓለማቀፉ ሸንጎ ምን ነካዉ ?/ የፈርግሰንና የኒዉ ዮርክ ክስ አጣሪ ዳኞች ጉድ ተጋባበት እንዴ ?/**

## አሜሪካ ዜጎቿን አስጠነቀቀች

አዲስ አበባ የሚገኘው የአሜሪካን ኤምባሲ ፣ መጪውን የምርጫ ድራማ ተከትሎ ድንገተኛ አመጽ ሊነሳ ስለሚችል ፣ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖሩትም ሆኑ ወደ ኢትዮጵያ የሚጓዙት ዜጎቹ ፣ አስፈላጊውን ጥንቃቄ እንዲያደርጉ አስጠነቀቀ።

እንደ ኤምባሲው ከሆነ ፣ በተለይ በዋና ከተማዋ አዲስ አበባ ውስጥ በመስቀል አደባባይ እና ቤልኤር እየተባለ በዘልማድ በሚጠራው አካባቢ ሰላማዊ ሰልፎች ሊደረጉና ሰልፉን ተከትሎም የህዝብ አመጽ ሊነሳ ስለሚችል እንደዛ ባሉ አደገኛ አካባቢዎች በጭራሽ መድረስ እንደሌለባቸው አሳስቧል። በተጨማሪም ምዕራባውያን በብዛት በሚገኙበት አካባቢ ፣ በትላልቅ ገበያዎች ፣ በቤተክርስቲያናት፣ በመስጊዶች ፣ በሆቴሎች ፣ ቡና ቤቶች እና በመሳሰሉት ስፍራዎች በሚንቀሳቀሱበት ጊዜ ልዩ ጥንቃቄ እንዲያደርጉም መክሯል። ከዚሁም ጋር አያይዞ የአልሻባብ ጥቃት በአካባቢው ሊደርስ እንደሚችልም ያለውን ስጋት ገልጿል።

በሌላም በኩል የአሜሪካ ዜጎችና ሠራተኞች ለደህንነታቸው ሲባል በኢትዮጵያ ውስጥ መጓዝ የሌለባቸውን አካባቢዎች የዘረዘረ ሲሆን ፣ ከነዚሁ ስፍራዎች ውስጥም የኢትዮ ኬኒያ የድምበር አካባቢ፣ ደቡብ ኢትዮጵያ፣ ወያኔ እና ሻዕቢያ ለጦርነት በሚፈላለጉበት ድንበር አካባቢ በአክሱም፣ በሽሬ በአዲግራት እና ከደሴ ወደሰመራ በሚወስደው መንገድ ፣ በጅቡቲ ፣ አፋር ውስጥ ደንከል በረሀ እና ኤርትራ ውስጥ በሚገኘው የእሳተ ገሞራ አካባቢ በኦጋዴን እንዲሁም በጋምቤላ ውስጥም ያለው ጸጥታ አስተማማኝ ባለመሆኑ ከስፍራው እንዳይደርሱ ሲል ለዜጎቹ ጥብቅ የሆነ ማስጠንቀቂያ አስተላልፎ ዜጎቹ ችግር ከገጠማቸውም አዲስ አበባ ከሚገኘው የአሜሪካ ኤምባሲ ጋር ግንኙነት ማድረግ እንዳለባቸው አስጠንቅቋል።

ፍኖተ ዴሞክራሲንና ፍኖተ ኅብረትን በቀጥታ በስልክ ማዳመጥ ይቻላል
ፍኖተ ዴሞክራሲ 401– 347– 0405
ፍኖተ ኅብረት 401-347-0175

## ሕዝባዊ ቁጣዎች በአዲስ አበባና በባህርዳር

*ሙስሊም ኢትዮጵያዊያን በአድስ አበባ ተቃውሟቸውን አሰሙ*
*በባህር ዳር ከተማ በተደረገ የተቃውሞ ሰልፍ በርካታ ንጹሀን ተገደሉ*

እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር ታህሳስ 10/2007 ወይም ዲሰምበር 19/2014 ዓ.ም የወያኔ የጸጥታ ሠራተኞች ሳይደርሱበት በጥንቃቄ የታቀደ የተቃውሞ ሰልፍ በሙስሊሙ ኢትዮጵያዊ ማህበረሰብ ሲደረግ ፤ በተመሳሳይ ቀን ደግሞ የባህር ዳር ከተማ ሕዝብ የአምልኮ ስፍራዬን አላስነካም ብሎ ከወያኔ ፋሺስት ወታደሮች ጋር ግብ ግብ ይዞ እንደነበር የሚታወስ ነው።

ከጥቂት ወራት በፊት በወያኔ የጸጥታ እና የፌዴራል ሀይሎች ለተቃዉሞ የወጣውን ሙስሊም ህብረተሰብን በከፍተኛ ድብደባ ደም በማፍሰስ ተቋርጦ የነበረው የዕለተ አርብ ተቃውሞ ፤ ድምጹን አጥፍቶ እና ኑር መስጊድን ማዕከሉ አድርጎ እንደገና በአስደናቂ ሁኔታ ተመልሶ ለበለጠ ተቀውሞ መዘጋጀቱን አብስሯል። ወያኔ ፣ ይህ አሁን የተደረገዉን የተቀውሞ ሰልፍ መደረጉን ቢያውቅ ኖሮ ፣ የጸጥታ ሀይሎቹን አሰማርቶ ድርጊቱን ለማስቆም ወደ ኋላ እንደማይል ፤ ከዚህ በፊት ከወሰዳቸው እና አሁንም ለተቃውሞ በሚወጡ ወገኖች ላይ እያደረሰ ያለው አፈና የሚያረጋግጥ ሲሆን ፤ ሁኔታወን የሚታዘቡ ወገኖች እንደሚሉት ከሆነ ግን ወያኔ እዛው አፍንጫው ስር ምን እየተደረገ እንዳለ እንኳ አለማወቁ ከፍተኛ ድንጋጤ ውስጥ ሊከተው እንደሚችል እንዲሁም ደግሞ በተቃራኒው የሙስሊሙ ማኅበረሰብ ተቀውሟቸውን በተቀነባበረ እና በተደራጀ መልክ እንደ አንድ ሰው ሆነው ሊያኪያሂዱ እንደሚችሉ የሚያሳይ መሆኑን ይናገራሉ።


በዚሁ ታህሳስ አስር በተደረገው የተቃውሞ ሰልፍ ፣ ሰልፈኛው ‘’ደምጻችን ይሰማ ፤ ለሂጃባችን እንሰጣለን ህይወታችንን ፤ ነጻነት ፍትህ ፤ በሀይማኖታችን አንደራደርም ፤...’’ እና የመሳሰሉ ሌሎችንም መፈክሮችን በአንድ ደምጽ ከማሰማታቸውም በተጨማሪ ፤ እነዚህኑ መፈክሮች በተለያዩ ቀለማት ባላቸው ፊኛዎች ላይ ተጽፈው ይታዩ የነበረ ሲሆን ፤ በመጨረሻም እነዚህኑ ፊኛዎች በአየር ላይ እንዲሳፈፉ በአንድነት ለቀዋቸዋል።

ሙስሊሙ ማህበረሰብ ከጥቂት ወራት በፊት በወያኔ የሀይል እርምጃ ድምጹን አጥፍቶ የቆየ በመሆኑ ምክንያት ከእንግዲህ ተቃውሞ የሚባል አይኖርም እያለ በአደባባይ ሲደነፋ ለነበረው ወያኔ ፤ ድንገት ‘’ድምጻችን ይሰማ!’’ እያለ እያስገመገመ አደባባይ መውጣቱ ፤ ለወያኔ ሀፍረት ብቻ ሳይሆን ፍርሀትም እንደሚሆን ለማንም ግልጽ እንደሚሆን አይጠረጠርም።

ይህ በእንዲህ እያለ በተመሳሳይ ቀን ባህር ዳር ውስጥ በጥምቀት በዓል ወቅት ታቦት የሚያድርበትን የአምለኮ ስፍራ ገንዘብ ካገኘ አገር ከመሸጥ የማይመለሰው ወያኔ ፤ ለልማት ይፈለጋል በሚል ሰበብ አካባቢዉን እንዲያፈራርሱ የላካቸውን አፍራሽ ግብረ ኃይሎች ፤ ሕዝቡ ስፍራውን አናስደፍርም ብሎ ያቆማቸው ቢሆንም ፤ ወያኔ ነፍሰ ገዳይ ወታደሮቹን በመላክ ወጣቶችን በመግደል እንዲሁም አዛውንቶችን በጥይት በመደብደብ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠላት መሆኑን እንደሁሌው ሁሉ በድጋሚ አስመክሯል።

በዚሁ የወያኔ የግድያ ድርጊት ከሰባት በላይ ወጣቶች ሲገደሉ እና ቁጥራቸው ያልተወቁ ሰላማዊ ዜጎች እና አዛውንተች የመቁሰል አደጋ ደርሶባቸዋል። በዕለቱም የከተማው ሕዝብ በነቂስ ወጥቶ ከወያኔ ፋሺስት ሠራዊት ጋር ግብ ግብ የገጠመ ሲሆን ፤ የሁለተኛ እና የከፍተኛ ደረጃ ተማሪዎች እንዲሁም ባጃጅ አሽከርካሪዎች ተቃዊሞውን ተቀላቅለዋል።

Rose Unisex Hair Salon (Tsegereda)
6222 Georgia Ave. NW Washington, DC.
20011



የሴቶችንና የወንዶችን፣ የልጆችንና የአዋቂዎችን ፀጉር እናስተካክላልን። ለቀለም ፣ለሹርባ፣ ለፀጉር ስፌትና ለፐርም ሰራ ባለሙያ ከፈለጉ Rose Unisex Hair Salon




ከኢሕኣፓ ጋር ለሚደረጉ ግንኙነቶች የሚከተሉትን መጠቀም የቻላል

| | |
|---|---|
| ስልክ፡ | (202) 291-4217 |
| ኢሜል፡ | espic@aol.com |
| ፖስታ፡ | EPRP<br>P.O. Box 73337<br>Washington, DC. 20056 |
| ድረ ገጽ፡ | eprp.com |

ፍኖተ ዴሞክራሲን ለማዳመጥ Finote.org

ከኢሕኣፓ ወክንድ (EPRPYL) ጋር ለሚደረጉ ግንኙነቶች የሚከተሉትን መጠቀም የቻላል

| | |
|---|---|
| ስልክ፡ | (202) 291-5832 |
| ኢሜል፡ | eprpylnew@gmail.com |
| ፖስታ፡ | EPRPYL<br>5309 Georgia ave.<br>Washington, DC. 20011 |
| ድረ ገጽ፡ | eprpyl.com |

## ደቂቀ ገሞራ

በዚህች በእኛ ምድር ፣ በዚህች በእኛ ሰማይ በኢትዮጵያ ከብዙ ከዋክብት ልቀው የሚታዩ ነበሩ፡፡ ዛሬም አሉ፡፡ እነዚህ ከዋክብት በዓለም አቀፍ ደረጃ ሰፊ እውቅና ካገኙት ከእነ ቪክተር ሁጎ፣ ከማክሲም ጎርኪ፣ ከሔሚንግዌ፣ ከአቼቤ፣ ከሶይንካ፣ ከማህፉዝ ናጉዪብ፣ ከፑሽኪን፣ ከቶልስቶይ፣ ከዲከንስ እንዲሁም ከመሳሰሉት ጨቋኝ ሥርዐቶች በሚያደርሱት ግፍ የጉስቁሉን ህዝብ መከራ በስነ-ጽሑፋቸው ፍንትው አድርገው እንዳሳዩት ሁሉ የኛዎቹ የኢትዮጵያ ከዋክብትም በብዕራቸው ባይልቅ የሚስተካከል በረከት አበርክተዋል፡፡ የጨቋኝ ሥርዐቶችን የሚገለማ ጠረን፣ የሚያሰጸይፍ ገጽታ፣ የሚዘገንን ጭካኔ፣ ጥርስ የሚያስነክስ አረመኔነት፣ በአጠቃላይ እኩይ ባህርያትን በብዕራቸው ተዋግተው የተዋጊውን ህዝብ መንፈስ ለትግል አነሳስተዋል፡፡ ዛሬም ድረስ እያነሳሱ ነው፡፡ ግን የነዚህ የኢትዮጵያ ከዋክብት ስም በበርካታ የብዙሀን መገናኛዎች አይወጋም፡፡ በአንዳንዶቹ ያውም የህዝብ ነን በሚሉ የብዙሀን መገናኛዎች በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ በሚደርስባቸው ተጽዕኖ የነዚህ ከዋክብቶች ስምና ሥራ በጨረፍታ እንኳ ሲወሳ ለማድመጥም ይሁን ለማንበብ አልታደልንም፡፡ ለአብተነት ለመጥቀስ የህማ ቱማ ድንቅዬ ግጥሞች፣ አጫጭር ልብ ወለዶች፣ ምጸታዊ የፖለቲካ ትችቶቹ ህዝባዊ ነን በሚሉ ድርጅቶች ድረ-ገጾች፣ ቴሌ ቪዥኖች፣ ሬድዮኖች፣ ጋዜጦች፣ መጽሔቶች እንዲሁም በስነ-ጽሑፍ ምሽቶች አለመቅረባቸው በእህህ ብቻ ታፍኖ እስከመቼ እንደሚቀጠል ግልጽ ሆኖ አይታይም፡፡ ለዴሞክራሲ እንታገላለን ከተባለ የህማን ሥራ ማቅረብ ሊታለፍ አይገባውምና በዓይነ ህሊናቸው አንጎላቸውን እንዲያነቡት በዚሁ አጋጣሚ እንዘክራለን፡፡

ዛሬ ገሞራው አረፈ ሲባል ስሙን ሲጠሩት ዓይኖቻችንን ከድነን ታዘብናቸው፡፡ አንደዜም ልሳናቸውን ከፍተው ማይምር ደብተራው ፀገየ ወይንን ወያኔዎች የት አደረሱት ሳይሉ ኢሕአፓ የጸገየ ወይንና የሌሎች ኢሕአፓዎች በወያኔ መገደላቸውን አስመልክቶ ያወጣውን መግለጫ ሲያነቡ ለሚሰማው መልስ አልባ እንቆቅልሽ እንደሚሆንበት ጥርጥር የለውም፡፡ ደብተራውና ገሞራው ከአንድ ምንጭ የተቀዱ ኩልል፣ ንጥር ፣ ጥርት ያሉ ውሀ ናቸው፡፡ ሁለቱም በግዕዝ ፣ በአማርኛና በእንግሊዘኛ እጅግ የመጠቀ ችሎታ ያላቸው በመሆናቸው ሊቀ ሊቃውንት ሊባሉ ይገባቸዋል፡፡ ሁለቱም በዜማ፣ በቅኔ ጥልቅ፣ ምጡቅና ባህር የሆነ እውቀት እንደነበራቸው ከሥራዎቻቸውና በቅርብ ከሚያውቋቸው መረዳት ይቻላል፡፡ በባህርያቸውም ቢሆን የሰውን ልጅ በማህበረ-ሰቡ ውስጥ ባለው ቦታ፣ በሀብቱ፣ በትምህርቱ፣ በእድሜው፣ በዘሩ ሳይሆን የሚያከብሩት በሰው ልጅነቱ ብቻ ነበር፡፡ የመኮፈስ፣ የአጉራ ዘለልነት፣ የአውቄ በቃሁነትና ባህርያት የሁለቱም ጠላቶች ናቸው፡፡ ታናናሾቻቸውን እንደ እኩዮቻቸው በማየት ሰርስሮ የሚገባ ፍቅርን የሚለግሱ ናቸው፡፡ እንኳን ለሰው ልጅ ለእንስሳትም ልባዊ ፍቅር ነበራቸው፡፡ ገሞራውና ደብተራው ቅኔዎቻቸው በረከትን በህዝብ መፈቀርንና መደነቅን እንዳጎናጸፏቸው ሁሉ መርገምንም አሳርፈውባቸዋል፡፡ በአጼው ዘመን ለእስር ተዳርገው ስቃይ መከራ ተቀብለዋል፡፡ ወገናቸው የኢትዮጵያ ህዝብ በጭቆና እየተገረፈ፣ ገበሬው በእንባ ዓይኖቹ እየሟሙ፣ ሠርቶ አደሩ አንጀቱ እየደማ ባለበት፣ ወታደሩ የአገሩ የወገኑ ዘብ መቆም ሲገባው ለጥቂቶች በመቆም ህዝብን አሳር በሚያሳይበት ሁኔታ ተድላና ደስታን እርግፍ አድርገው ሳይሸራርፉ ሙሉ ህይወታቸውን ለጉስቁሉ ለኢትዮጵያ ህዝብ ሰጡ፡፡ የቅኔ ዘረፋ፣ የመወድስ ድርደራ ከነዚህ ከዋክብት በላይ ለማን ይደረጋል፡፡

ዕድለኞች አሉ፣
ወለም ዘለም ያላሉ፣
የወገናቸውን ሰቆቃ መከራ ሊከሉ፣
ሎጋ ህይወታቸውን፣
ምትክ አልባ ነፍሳቸውን፣
ከአንጀት ለሚወዱት፣
ተድላ ደስታውን ሊያጎናጽፉት፣
ገና በማለዳ አሀዱ ሲል፣
አሏህ ወአክበር ሲባል፣
የቅኔያት ዘር ዘሩ፣
እኔን፣ አንተን፣ እሷን ኮረኮሩ፣
ተከላቸው ፀገየ-አበበ፣
ጥቁር ጥላን በአይኬዎቹ ላይ ደበበ፣
ፀሐይ ለአፈር-ገፊው፣
ለተራበው ለተጠማው፣
አንጀቱ የታጠፈውን ለመታደግ፣
ለከሲታው ለአፈርማው፣ ብርሀኗን ፈንጠቅ ስታደርግ፣
ተጋረደ በምራጭ ወታደሩ በደርግ፡፡
የፀገየው ፍሬ ፍራፍሬ፣
የተዘራው ጥሬ ጥራጥሬ፣
አቤት ሲያምር እርሻ ምልቶ፣ ከአገር እስከ ዳር ሰርፍቶ፣
ቀነየ ቀነየ ሳብ እረገብ፣
ሲዘምሩ ሲያዜሙ ዋ! እያሉ፣
ተምቾች አበቦችን ቀነደሉ፣
የአበቡ የፀገዩትን ሁሉ፣
ምን ቢንደላቀቁ ምን ቢበለጽጉ፣
ምን ቢወሻከቱ ምን ቢመላገዱ፣
የፀገየ ገሞራ ከቶ አይቀርላቸው፣
አቃጥሎ፣ አንድዶ፣ አንኮሮ ይፍጃቸው፡፡

የፀገየ ደብተራው **ናስተማሰለኪ**፣ የኃይሉ ገሞራው **በረከተ መርገም** የተጻፉት የአጼውን ዘመን ግፍ ለማሳየትና ለመርገም ለመኮነን ነበር፡፡ ድምጻቸው ዛሬም ድረስ ያስተጋባል፡፡ ዛሬም አገራችን ኢትዮጵያን **ናስተማሰለኪ**ስንል አንድ ከመቶ የማይሞሉት ወያኔዎችንና አጉራ ዘለል አጫፋሪዎቻቸውን ሳይሆን ከመቶው ዘጠና ዘጠኝ የሚሆነውን ጉስቁል፣ ምዝብር፣ በረሀብ፣ በበሽታ፣ በፊደል ጥማት የሚሰቃየውን ማለት መሆኑ ደምቆ ይሰማል፡፡ ቀኝ ጌታ ዮፍታሄ ንጉሤ በጣሊያን ወረራ ዘመን በስደት በነበሩበት ወቅት የቋጠሯቸው ስንኞችም እንዲሁ ለዛሬው የጠባቦቹ የጭቆናና የግፍ ዘመን ያስተጋባሉ፡፡
ረሀቤ ጥሜ እርዛቴ ሦስቱ፣
ይደበድቡኛል በአንድ እየዶለቱ፡፡
በዚህ ሃያ አንደኛ በሚባለው ዘመን በዓለም የአንደኝነት ደረጃን አትንኩብኝ በሚለው በአምባ ገነኑና በአረመኔው ወያኔ በፍትህ ርትዕ ላይ የተመሰረተ የሀብት ክፍፍል ባለመኖሩ ጥቂት ሀዳጣኖች በሚሊዮን ቁንጣን እቅብ እቅብ በመተንፈስ ሲሰቃዩ፣ ህልቆ መሳፍርቱ ህዝብ በጠኔና በችጋር በነፍስ ውጪ በነፍስ ግቢ ህይወት ይማቅቃል፡፡ ገሞራው በ**በረከተ መርገም** ባነሳቸው ጭብጦች ጠቅለል ተደርገው ሲታዩ የሰው ልጅ በአድጉቱ፣ በሥልጣኔው የፈለሰፋቸው ቁሶችና የፈለሰማቸው ይትበሀሎች ለሰው ልጅ ጠቀሜታነት መዋላቸው ቀርቶ ለሰው ልጅ ጥፋትና ውድመት መዋላቸውንና ይህን እኩይ ድርጊት አስፈጻሚና ፈጻሚዎችን ኮነነ፡፡ አረገመ፡፡ ውጉዝ ከመ አርዮስ አላቸው፡፡ እንደ አርዮስ ይለዩ ይረገሙ፡፡ ዝነኛው፣ አንጋፋው ዘፋኝ ዓለማየሁ እሸቴ ያቀነቀነው ፀረ - ኮሎኒያሊዝም የሆነው **ያ ጥቁር ግሥላ** የተሰኘው ግጥም የደብተራው የጸገየ ወይን ነው፡፡ ስንኞቹ የጸገየ ወይንን የመጠቀ ቅኔ ዘራፊነት ይመሰክራሉ፡፡

**በረከተ መርገም** ዛሬም ድምጹ በቅኔው ማህሌት በተዘረፈበት ዘመን ሳይቀነበብ በዛሬው ግፈኛ፣ ዘራፊ፣ ዘረኛና ደም አፍሳሽ የሆነው ወያኔንም ከነግፉ ከነግሳንሱ ነፋሪት ያንፍርህ ይለዋል፡፡ ነገም በህዝብ ስም በዴሞክራሲ ስም ሥልጣን ኮርቻ ላይ ፊጥ ለማለት አንዴ ለአሜሪካ፣ ሌላ ጊዜ ለአውሮጳ ብዙ ጊዜ ለሸአቢያ የሚያጎነብሱትን፣ የነጭ ነጫጭባን ጫማ የሚልሱትንም ነጎድጓድ መብረቅ ይባርቅባችሁ ይላቸዋል፡፡ በምዕራቡ ዓለም የፖለቲካውን ሞተር የሚዘውረው በህዝቡ ተመረጠ የሚባለው መንግስት መሆኑ ቀርቶ የነጋዴዎን ኃይል መሆኑን በመረዳት ይመስላል ጥቂት የማይባሉ ምሁንድስና፣ ምጣኔ-ሀብት፣ ህክምና የተማሩ ሊቂቃን በምዕራብ አገራትና በአገር ውስጥ ህጋዊ ተብዬ ድርጅት መሪዎችን ገሞራው ከመጠምጠም መማር ይቅደም፣ አሻፈረኝ ካሉም የዳሎል ገሞራ አቃጥሎ ይፍጃችሁ ይላቸዋል፡፡ በጋዜጠኝነት ስም የቀጣሪያቸው አገልጋይ በመሆን ሲጠሯቸው አቤት ሲልኳቸው ወዴት የሚሉ ምርኮኛ ለሆዳቸው ለከርሳቸው ያደሩትን እንደ ጋሪ ፈረስ የሚጋለቡትን ጋዜጠኞች እግዚአብሔር መልሶ በየእናታቸው ማህጸን ይቆልፍባችሁ ይላቸዋል ገሞራው፡፡ ገበሬውን ደም ዕምባ የሚያስነቡትን፣ የሀጻናት ጉልበትን የሚያስበዘብዙትን፣ ልጃገረድ እህቶቻችንን ለአረቦች እየፈነገሉ የሚሸጡትን፣ ለሠራተኞች አግባብ ያለው ደሞዝ የማይከፍሉትን አውሎ ነፋስ ጠራርጎ እንጦርጦስ ያውርዳችሁ ያላቸዋል ማይዕምር ገሞራው፡፡ የአማራ ገበሬን በማገንቱ ብቻ ከእርሻውና ከቀየው የሚያፈናቅሉትንና ህጻናቱን የሚያርዱትን፣ እናትና ልጆችን የሚደፍሩትን፣ ለድንበር ዘለል የባዕድ የእርሻ ከባንያዎች የጋምቤላን፣ የኦሮሞን፣ የመገንግር፣ የአማራን ገበሬዎች ያፈናቀሉትንና በጥይት የረሸኑት ወያኔዎችን ንፍር ውሀ ያንፍራችሁ ፡፡ መሸሺያ መሸሸጊያ አይኑራችሁ ዘንዶ ይዋጣችሁ ይላቸዋል ገሞራው፡፡ ወያኔዎች ትምህርትን በአፍጢሙ ደፍተውትና ተረግጠውት እንደገና መልሰው ትምህርትን እናጠራለን እያሉ በኢትዮጵያ ህዝብ ልጆች ላይ በመዘበታቸው ገሞራው የዱር አንበሶች ቦጭቀው ቦጫጭቀው አንክተው ይፍጇቸው ይላቸዋል፡፡ ህክምናና መድሀኒትን እንደ ሰማይ እርቀውበት በተለያዩ ደዌዎች ህዝቡን ለአልጋ ቁራኛ የዳረጉ፣ እናቶችን ከወሊድ ጋር በተያያዘ ሞታቸውን የሚያጣድፉትን፣ ህጻናትን በበሽታ የሚቀጩትን፣ አረጋውያንን በበሽታ አማቀው የሚገድሉትን፣ ወጣቶችን በተለያዩ ሱሶች የሚያስለክፉትንና በበሽታ እድሜያቸውን የሚቀጩት ወያኔዎችን የአንበጣ መንጋ በመርዝ ይፍጃቸው፡፡ ሙጥጥ ያርጋቸው ብሏል ገሞራው፡፡ ለከርሳቸው ለሆዳቸው ሲሉ ለአረመኔው ወያኔ ያደሩ አድር ባዮችን የቆማችሁበት ምድር ተከፍቶ ይዋጣችሁ ብሎ ገሞራው መረቃቸው፡፡ በሀይማኖች አባትነት በሙስሊሙም በክርስቲያኑም በወያኔ የተሾማችሁ በሀይማኖት ስም የምታመነዝሩ ጳጳሳት ቀሳውት ወሼሆች በቁማችሁ የንፍር ውሀ አንኮሮ ቀቅሎ ሙክክ ያድርጋችሁ እያለ ገሞራው አረገማችሁ፡፡ ለአረመኔው መለስ ያለቀሳችሁ ዘፋኞች፣ ያነባችሁ ከያኔዎች፣ ደረት የደቃችሁ የማስታወቂያ ጡሩምባ ነፊዎች፣ ለሆዳችሁ ብላችሁ ዓይናችሁን የጨመቃችሁ ዶክተር መምህራን ወሐኪሞች ገሞራው የሎስ ስንጥቅጥቅ ያርጋችሁ ብሎ አከበራችሁ፡፡ የሀሰት የእድገት ቁጥር የምታወሩ አለቃ ወምንዝር ወያኔዎች እንዳች አዙሪት አዙሮ አዙሮ ገሞራው ፍግም ድፍት ያድርጋችሁ ብሎ አሞካሻችሁ፡፡ በነጻ ጋዜጣ ወመጽሔት ስም የምታደናግሩ የወያኔ ሪፖርተሮች፣ ፎርቹኖች ወሌሎችም ከየግድግዳው ለትሞ አጋጭቶ ይድፋችሁ በሉልኝ ብሏል ገሞራው፡፡
ፀገየ ወይንና ገሞራው ድምጻቸው አንድ ነው፡፡ ሁሌም ዋ! ዋ! ዋ! እያለ ይጮኻል፡፡ እነዚህ ሁለት ከዋክብት የበርካታ ከዋክብት ወኪሎች ፋና ወጊዎች ናቸው፡፡ ዘራቸው ፀገዩቶ፣ አብቦ፣ አፍርቶ መጎምራቱ አይቀሬ ነው፡፡ የበሰለው ፍሬም ለህዝቡና ለህዝብ ልጆች አብነት ሲሆን ለህዝብ ጠላቶች ግን ገሞራ ነው ፡፡ ያቃጥላል፡፡ ያንጨረጭራል፡፡

## ጎሞራው ሄደ አሉ ሳይሰናበተን

አሥራደው (ከፈረንሳይ)

በገንዘብ ሲኮራ - ሰው በወርቅ ሲያጌጥ፤
ጎሞራው በቅኔ - ነበር ይንቆጠቆጥ፤
ኩታው ነበር ቃላት - ካባው ነበር ስንኝ፤
ጎሞራው ሲቋጥር - ለወገኑ ሲቀኝ፡፡
ሄዮ አሉ ጎሞራው - ሁሉን ነገር ንቆ፤
ሊቀኝ ቅኔ ሊዘርፍ - ከዚች ዓለም ርቆ፡፡

ሃቅ ነበር ጋሻው - ቃላት ነበር ጦሩ፤
ቡዮል ኮሶው ሲሆን - ሰብዕና ነው ክብሩ፤
ጥበብን ኩታ አርጎ - ቃላት እንዮ በትር፤
ነብስ እያስጨነቀ - ሥጋን የሚመትር፤
ከቆዳ ስር ዘልቆ - ልብ የሚቦረቡር፤
ጠጣሩ እንዲላላ - የላላ እሚወጥር፤
ያጥቢያ ፋኖ ወጊ - የብዕሩ ነብር፤
ጎሞራው፤ ጎሞራ፤ - ጎሞራ! ነበር፡፡

እያንገጫገጨ - ምጁት የሚነሳ፤
ቃላት እየዘራ - ሃሳብ የሚያወሳ፤
ጠጣር ያ'ረግ አለት - የቋንቋ ወዝ ቅባት፤
ጉንጉን ያ'ሳብ ቅኝት - ሽርብርቦሽ ቃላት፤
በእሳት ተፈትኖ - ፈልቶ ሲወጣ ቃል፤
የኑዮዮው ጨሶ ያረረው ይስቃል፡፡
"ጎሞራው ሄዮ አሉ ሳይሰናበተን፤
እንሸኘው ነበረ - ምንም ቢታክተን"፡፡

ሃሳብ የሚያዋልድ - የሚያጭር ብልጭታ፤
ድንበር ሳይገድበው - በሄደበት ቦታ
አሳቢ ለወገን - ቋሚ ዋልታ ላገር፤
ጎሞራው ዝም አለ ዳግም ላይናገር፡፡
" አገሬ ኢትዮጵያ ታጠቂ በገመድ፤
ጎሞራው ባዳ እንጂ አይቀብረውም ዘመድ"፡፡
ጎሞራው ባዳ እንጂ አይቀብረውም ዘመድ"፡፡

**ለዕውቁ የስነ ጽሁፍ ሰው: ደራሲና ገጣሚ ኃይሉ ገብረዮሐንስ፤ ጎሞራው ማስታወሻ: የተቋጨች:: ሕዳር 6 ቀን 2007 ዓ.ም. (November 15/2014)**

# ዴሞክራሲያ

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን

ዴሞ ቅጽ 40 ቁ. 2 ኅዳር 2007 ዓ.ም


## የአገራችን ሁኔታ ምን ይመስላል? ምንስ መደረግ አለበት?

ወያኔ ሥልጣን ከያዘ ጀምሮ የነበረው ሁኔታ ከዚህ ቀደም በተደጋጋሚ የተገለጸና አሁን በአገር ውስጥ ያለውም ሁኔታ ለብዙ ዜጎች በግልጽ የሚታይ ቢሆንም የአገራችንን ሁለንተናዊ ሁኔታ በየጊዜው እየዳሰሱና እየገመገሙ አጠቃላይ ግንዛቤ መያዝ የወደፊቱን አቅጣጫ ለመቀየስ ይረዳል። ስህተትና ድክመትን አርሞ ጠንካራ ጎንን አፈርጥሞ ትግሉን ወደፊት ለማስኬድና ግቡን እንዲመታ ለማድረግ ያስችላል። በመሆኑም የወቅቱ የዴሞክራሲያ ዕትም የጊዜውን ሁኔታ በመመርመርና የወደፊቱን አቅጣጫ በመጠቆም ላይ ያተኩራል።

የዛሬ 23 ዓመት በጠመንጃ ኃይል ሥልጣን የያዘው የወያኔ ቡድን አሁንም ሥልጣኑን በቁጥጥሩ ስር አድርጎ ይገኛል። በእነዚህ ዓመታት የወያኔ የሥልጣን ማእከል ከቡድን ወደ ግለሰብ እንደገናም ወደ ቡድን እየተንከባለለ የቆየ ቢሆንም የአገዛዙ አምባገነንነትና ፈላጭ ቆራጭነት ለአፍታም የደበዘዘበት ጊዜ አልነበረም።

በምዕራባውያን ድጋፍ እና በአረቡ ዓለም ርዳታ እንዲሁም በሻዕቢያና በሱዳን ትብብር በወታደራዊ ኃይል፤ በገንዘብና በድርጅት ተጠናክሮ የጎለመሰው የወያኔ ቡድን ከሥልጣን ኮርቻ ላይ ሲቆናጠጥ አገዛዙ ከአምባገነነት እንደማያልፍ ግልጽ ነበር። ቀደም ብሎ ሲያንጸባርቃቸው ከቆዩት አቋሞቹና ሲያደርጋቸው ከነበሩ ቅስቀሳዎች ወታደራዊ ኃይሉን ተጠቅሞ ለረጅም ዓመታት አምባገነን አገዛዙን ለማስፈን ፍላጎትና ጽኑ እምነት እንደነበረው ይታወቅ ነበር። ሥልጣን በያዘበት ወቅት የሕዝብ እምቢተኛነትና የዴሞክራሲያዊ ድርጅቶች እንቅስቃሴ ስጋት ውስጥ ጥለውት የነበሩ መሆናቸው የማይታበል ቢሆንም በወሰዳቸው የማስመሰያ እርምጃዎች፤ እንዲሁም በአንድ በኩል በጥቅም በደለላቸው በሌላ በኩል ውዥንብር ውስጥ በገቡ ድርጅቶችና ግለሰቦች ተባባሪነት ስጋቱን አስወግዶ ሥልጣኑን ለማደላደል በቅቷል። በወያኔና በሻዕቢያ ተወጥኖ የምዕራብ አገሮችን ቡራኬ ያገኘው የማስመሰያው የሽግግር ጉባኤ በርካታ ጸረ አንድነትና ጸረ ኢትዮጵያ የሆኑ ጉዳዮችን ከመወሰኑ በተጨማሪ ወያኔ የበላይነቱን ያጠናከረበት ውሳኔ አጽድቆ ተበትኗል። የሽግግሩን ወቅት በበላይነት የሚመራበትን፤ የወያኔ ጦር የኢትዮጵያ ጦር ሆኖ በበላይነት የሚሰየምበትን፤ ጸጥታውንና የመንግሥት አውታሮችን ሙሉ በሙሉ በወያኔ ድርጅት ቁጥጥር ውስጥ የሚወድቁበትን፤ አገሪቱ በዘር ክልል ተከልላ የሕዝቡ አንድነት ለዘለቄታው የሚዳከምበትን ሁኔታ ወስኖ ተለያይቷል። በሽግግሩ ዓመታትም ወያኔ ጉባኤው የሰጠውን ሕጋዊ ሽፋን ተጠቅሞ ሥልጣኑን ለማጠናከርና ለመደላደል ችሏል። "ዴሞክራሲያዊ እርምጃዎችን እየወሰደ ነው"፤ "ጊዜ እንስጠው"፤ "ሕዝብ ጦርነት ሰልችቶታል"፤ "ወያኔን የሚቃወም የቀድሞውን ናፋቂ ነው"… ወዘተ በማለት እንደ ኢሕአፓ ዓይነቶችን ታጋይ ኃይሎች አፍ ለማዘጋት ይፍጨረጨሩ የነበሩትና ለወያኔ ሽፋን ሆነው ሲያገለግሉ የቆዩት ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ስህተት መፈጸማቸውን አውቀው ከሽግግር መንግሥት ቢወጡ፤ ከተከታታይ ምርጫዎች ራሳቸውን ቢያገሉ፤ አንዳንዶቹም ጠመንጃ ይዘው ለመዋጋት ቢሞክሩ፤ የምዕራብ ኃይሎችን ቢማጸኑ፤ በምርጫዎች ወያኔን ለማሸነፍ ከፍተኛ ርብርቦሽ ቢያደርጉና የመሳሰሉትን እርምጃዎች ቢወስዱ ወታደራዊና ድርጅታዊ ኃይሉን አጠናክሮ ሥር የሰደደውን የወያኔን ኃይል ሊገረሥሱት ቀርቶ ሊነቀንቁት አልቻሉም። የመንግሥት ተቋሞችን በተለይም የወታደራዊውንና የጸጥታውን ተቋም አንድ ኃይል በብቸኝነት በተቆጣጠረበት ሁኔታ የሕግ የበላይነት፤ ነጻ ሚዲያ፤ የሕዝብ መብት መረጋገጥ፤ ነጻና ፍትሐዊ ምርጫ፤ …ወዘተ ትርጉመ ቢስ መሆናቸው ግልጽ ነበር።

ስለሆነም በዛሬዋ ኢትዮጵያ የፓለቲካ ሁኔታም የዛሬ 23 ዓመት የተዘረጋው የአንድ ቡድን አምባገነን አገዛዝ ተስፋፍቶና ተጠናክሮ ቢታይ ብዙ የሚያስገርም አይሆንም። ዛሬ የዜጎች ዴሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብቶች ሙሉ በሙሉ ታፍነዋል። ከ40 ሺህ በላይ የሚሆኑ ዜጎች በፖለቲካ አመለካከታቸው ወይም አገዛዙን በመቃወማቸው ብቻ በተለያዩ እስር ቤቶች ታጉረው እየተሰቃዩና ኢሰብዓዊ ድርጊት እየተፈጸመባቸው ይገኛሉ። በሺዎች የሚቆጠሩ በአገዛዙ ታፍነው የደረሱበት ጠፍቷል። ሀሳብን በነሳ የመግለጽ፤ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅት ፈጥሮ በግምባር ቀደምትነት የመንቀሳቀስ፤ በሰላማዊ ሰልፍና መሰል እንቅስቃሴዎች የወያኔን አገዛዝ የማውገዝ፤ ተቃውሞ የማሰማት መብቶች ለይስሙላ አሉ ቢባልም በሽብርተኛነት የሚያስከስሱና በአነስተኛው ለብዙ ዓመታት እስራት ፍርድ የሚያሰጡ መሆናቸውን እያየን ነው።

ዛሬ ወያኔ ሥልጣኑን የሚጠብቁትንና የሚከላከሉትን የአፈና ተቋሞች የጦሩንና የጸጥታ ኃይሉን በባለቤትነት ያሽከረክራል። ለአገዛዙ ደጋፊና ተባባሪ የሆኑትና ቢሮክራሲውን፣ የፍርድ ተቋሙን፣ የይስሙላ ምክር ቤቱን፣ …ወዘተ በበላይነት ይመራል፤ ይቆጣጠራል። በተጨማሪም የኢትዮጵያን ሕዝብ የጅምላ እስር ቤት የሚያደርጉ የተለያዩ የቁጥጥር ዘዴዎች ቀይሶ ተግባራዊ አድርጓል። አንድ ለአምስት የሚል የፈጠረው የአደረጃጀት ስልት የስለላ ተግባር ለማከናወንና ሕዝብን አሸማቆ እንገቱን ለማስደፋት እየተጠቀመበት ይገኛል። ከምዕራብ አገሮች በገፍ የሚሰጠውን ገንዘብ በማፍሠስ ከስድስት ሚሊዮን በላይ አባላትና ሰላዮችን መልምሎ ለአጫፋሪነት እየተጠቀመባቸውም ይገኛል።

የሙያ ማኅበራትን፣ የሃይማኖት ተቋማትን፣ የሲቪክ ድርጅቶችን፣ በተቃዋሚ የሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ድርጅቶችን፣ ...ወዘተ ሰርጎ በመግባትና ቁልፍ ቁልፍ ቦታዎችን በመቆጣጠር ተቋሞቹ የወያኔ ፖሊሲ አስከባሪና አገልጋይ እንዲሆኑ ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት ያደርጋል። በገጠር ተቃዋሚ ተብሎ የሚጠረጠር አርሶ አደር የእርዳታ እህልና ማዳበሪያ ይነፈጋል። የአገዛዙ ተቃዋሚ ተብለው የተፈረጁ ተማሪዎች ወደ ከፍተኛ ተቋማት የመግባት እድላቸው ይዘጋል፤ የተቃዋሚ ድርጅቶች አባላት ወይም ደጋፊዎች የተባሉ ዜጎች የሥራ ዕድል ይነፈጋሉ፤ የወያኔን ፖሊሲ የተቃወሙ ነጋዴዎች የንግድ ፈቃዳቸውን ይነጠቃሉ ወይም ታክስ ይቆለልባቸል። ባንጻሩ ለአርሶ አደሩ እህልና ማዳበሪያ፤ ለተማሪዎች የትምህርት እድል ለሥራ ፈላጊዎች የሥራ እድል፤ ...ወዘተ በመስጠት ወያኔ በርካታ አባሎችንና ደጋፊዎችን ለማፍራት ተንቀሳቅሷል። ዛሬ ወያኔ የፖለቲካውን መድረክ በብቸኝነት በበላይነት በመቆጣጠር የሕዝብን መብት ገድቦና አፍኖ አምባገነን አገዛዙን አስፍኖ ይገኛል።

ዴሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብቱ ታፍኖ በትልቅ ስቃይ የሚኖረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከእጅ ወደ አፍ የሆነው የኑሮ ሁኔታውም ከጊዜ ወደ ጊዜ እያሽቆለቆለ ሄዶ መኖር ከማይችልበት ጠርዝ ላይ እየደረሰ ይገኛል። "የአገሪቱ ኢኮኖሚ አደገ ተመነደገ፤ የድርብ አሃዝ እድገት አሳየ፤ በቅርብ ዓመታት ውስጥ ኢትዮጵያ ምድቧ መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ምድብ ይሆናል የሚሉ" የተጋነነኑ አነጋገሮችና ጩኸቶች በፉከራዎችና ቀረርቶዎች ታጅበው በወያኔ ባለሥልጣናት ሲስተጋቡ ማዳመጥ ከጀመርን ከአስርተ ዓመታት በላይ ሆኖናል። የኢኮኖሚው አድገት አሃዝ በምዕራቡ ዓለም መንግሥታትና በዓለም አቀፍ ድርጅቶችም በተደጋጋሚ ሲስተጋቡ ቆይተዋል።

በሜዳ ላይ ያለው እውነታ ግን ከዚህ የተለየ ነው። አሁንም አገራችን አብዛኛው ዜጋ በከፍተኛ ችግርና ድኽነት የሚኖርባት፤ በዓለም ላይ ካሉ ደኻ አገሮች መካከል በመጨረሻው ተርታ ተሰልፋ የምትታይ አገር ናት። በእርግጥ ባለፉት ጥቂት ዓመታት በአገልግሎት ዘርፍ ውስጥ የሚጠቃለሉ አንዳንድ የእድገት እንቅስቃሴዎች ተደርገዋል። መንገዶች ተሰርተዋል፤ ድልድዮች ተገንብተዋል፤ የኤሌክትሪክ ምሰሶዎች ተተክለዋል፤ ሌሎችም የግንባታ ሥራዎች ተሠርተዋል። በአዲስ አበባና በሌሎች ከተሞች በርካታ የንግድና የመኖሪያ ሕንጻዎች ቆመዋል። የነዚህን ግንባታዎች ወጭ የሸፈነው ወያኔ ያመረተው ሀብት ሳይሆን ከጨቅላነቱ ጀምሮ በገንዘብ፤ በወታደራዊ መሳሪያ፤ በሃሳብና በምክር እያጠናከሩ ለሥልጣን ያበቁት ምዕራባውያን ታይቶ በማይታወቅ ደረጃ በሰጡት የገንዘብ እርዳታና እንዲሁም እንደቻይና ያሉ አገሮች ለጥቅማቸው ሲሉ ባጎረፉት ከፍተኛ ብድር ነው።

ወያኔ ሥልጣን ከያዘ ጀምሮ ምዕራባውያን ለወያኔ ከ35 ቢሊዮን ዶላር በላይ የሚሆን ገንዘብ በርዳታና በብድር ስም የሰጡ ሲሆን ከጥቂት ዓመታት ወዲህ ደግሞ በዓመት በአማካይ 3.5 ቢሊዮን ዶላር ሲሰጡ ቆይተዋል። በዓመት ለወያኔ የተሰጠው የእርዳታ መጠን ከአፍሪካ ውስጥ የመጀመርያውን ደረጃ የያዘ ሲሆን ከ50 እስከ 60 ከመቶው የሚሆነውን የወያኔን ዓመታዊ የመንግሥት በጀት የሸፈነ ነው። የምዕራብ አገሮች ይህን ያህል እርዳታ የሕዝብ ተቀባይነትና መሠረት ለሌለው ለወያኔ ቡድን ያፈሰሱበትን ምክንያት ለማወቅ ጠንቋይ መሆንን አይጠይቅም። ምዕራባውያን ለረጅም ዘመናት በርካታ ገንዘብና ሀብት አፍሰው ለሥልጣን ያበቁት ድርጅት ሥልጣኑን አደላድሎ፣ አስተማማኝ አድርጎ፣ ቀውስን አስወግዶ ጥቅማቸውን እንዲያስጠብቅላቸው ይፈልጋሉ። እግሩን ሳይተክልና አገዛዙን ሳያጠናክር በተለያዩ ቀውሶችና በሕዝባዊ እንቅስቃሴ ቢወገድ የገፈገፉት በርካታ ገንዘብና ድካም ከንቱ ሊቀር ነው ማለት ነው። ስለሆነም ከፍተኛ እርዳታ በማድረግ ከቀውስ ጠብቀው ህይወቱን ለማዳን ሞክረዋል። ይኽም ሆኖ ግን ወያኔን የቀውስና የአለመረጋጋት ስጋት ካለባቸው የዓለም አገሮች አንዱ ሆኖ ከመፈረጅ አላዳኑትም። ቻይናም በአንድ በኩል ርካሽ ሸቀጧን ለማራገፍ በሌላ በኩል ጥሬ እቃዎችንና ሌሎች የተፈጥሮ ሀብቶችን በርካሽ ለማጋበስ እንዲሁም ጥራታቸው አስተማማኝ ባልሆኑ ፕሮጀክትና በመሳሰሉት የሥራ መስኮች በመሳተፍ ከፍተኛ ብዝበዛ ለማካሄድ ባለፉት ዓመታት መጠኑ ከፍተኛ የሆነ ብድር ሰጥታለች። ቻይናም በአንድ በኩል ርካሽ ሸቀጧን ለማራገፍ በሌላ በኩል ጥሬ እቃዎችንና ሌሎች የተፈጥሮ ሀብቶችን በርካሽ ለማጋበስ እንዲሁም ጥራታቸው አስተማማኝ ባልሆኑ ፕሮጀክትና በመሳሰሉት የሥራ መስኮች በመሳተፍ ከፍተኛ ብዝበዛ ለማካሄድ ባለፉት ዓመታት መጠኑ ከፍተኛ የሆነ ብድር ሰጥታለች። በ 2013 ዓ.ም ወያኔ ከውጭ በብድር ካገኘው ገንዘብ ውስጥ 69 ከመቶ የሚሆነውን ያገኘው ከቻይና ነው።

ከላይ ከተጠቀሰ ገንዘብ ሌላ በዓመት ወደ 1 ቢሊዮን ዶላር የሚገመት ገንዘብ ውጭ ከሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ወደ ውስጥ ይገባል። ይህ ሁሉ ገንዘብ በውጭ ምንዛሬ ወደ አገር ውስጥ ሲገባ የተወሰነ የኢኮኖሚ እድገት ማስገኘት እንደሚችል የሚያጠራጥር አይደለም። ይሁን እንጅ የወያኔ ጣራ የነካ ፕሮፓጋንዳን ወደ ጎን ትተን ውስጡን ስንመረምር ተደረገ የተባለው የአሃዝ እድገት በአብዛኛው በአገልግሎት ሰጭ ዘርፍ መሆኑንና ጠቅላላ ኢኮኖሚውንና የሕዝቡን የኑሮ ሁኔታ ለመለወጥ ገና ብዙ፣ ብዙ የሚቀር መሆኑን እንረዳለን።

በኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የአሃዝ እድገት የዜጎችን የኑሮ ሁኔታ እስካልቀየረ ድረስ አሃዝ ሆኖ ብቻ ይቀራል እንጅ ፋይዳ ሊኖረው አይችልም። የኢኮኖሚ እድገት ተደረገ ተብሎ ከበሮ በሚደልቅባት አገር የሕዝቡ የኑሮ ሁኔታ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል። በተባበሩት መንግሥታት የሕዝብ የኑሮ እድገት መለኪያ መሠረት (ማለትም በትምህርት፤ በጤናና በሌሎች የኑሮ ሁኔታ መለኪያዎች) ዛሬም ኢትዮጵያ ከ 187 አገሮች ውስጥ 173ኛውን ደረጃ በመያዝ በዓለም የመጨረሻ ተርታ ተሰልፋ ትገኛለች። 73 ከመቶ የሚሆነው የአገራችን ሕዝብ በቀን ከ$2 ዶላር በታች ገቢ የሚያገኝ ነው። በቀን 1.25 ዶላር የሚያገኘው ብዛት ከሕዝባችን 35 ከመቶ የሚሆነው ነው። 88.2 ከመቶ የሚሆነው ሕዝብ በጤና በትምህርትና በኑሮ ሁኔታ የመጨረሻ ደኻ ተብሎ የተፈረጀ ነው። ከሕዝባችን 72 ከመቶ የሚሆነው በተራቆተ መሬት ላይ የሚኖር ነው። 44 ከመቶ የሚሆኑት ሕጻናት በቂ ምግብ የማያገኙ ናቸው። በገጠር የምግብና የእህል እጥረት ከፍተኛ ነው። አሁንም አገራችን ራሷን መመገብ አቅቷት የእርዳታ እህል ተቀባይ ሆና ቀርታለች። በያዝነው 2014 ከአሜሪካ እርዳታ ድርጅት (US Aid) ብቻ የ$237 ሚሊዮን (ዶላር) የምግብ እርዳታ ተቀብላለች። በከተሞች በአነስተኛ ደረጃ የተሟላ የመጸዳጃ አገልግሎት የሚያገኘው ሕዝብ 27 ከመቶ ብቻ ነው። የኢንተርኔት ተጠቃሚው ከሕዝብ 1.5 ከመቶ ብቻ ነው። ከተሞች አካባቢ በመብራትና በውሃ እጦት የሚሰቃየው ሕዝብ ቁጥር ከፍተኛ ነው። በዋና ከተማው ዛሬ መብራት ለሳምንታት ያህል ጨርሶ የሚጠፋበት ሰማይ ጠቀስ ፎቆች በተንጣለሉበት ከተማ ወሃ በጀሪካን የሚገዛበት ጊዜ ደርሰናል።

በደሃውና በሃብታሙ መካከል ያለው ልዩነት ከፍተኛ ነው። የወያኔ ባለሥልጣናትና ከፍተኛ መደብ ውስጥ የሚጠቃለሉት ክፍሎች በሚያገኙት ከፍተኛ ደሞዝና በዝርፊያ በሚያግበሰብሱት ገንዘብ በድሎትና በምቾት ሲኖሩ መካከለኛና ዝቅተኛ ገቢ የሚያገኘው የኅብረተሰብ ክፍል ደግሞ ከእጅ ወደ አፍ በሆነ ሆኔታ እንዲኖር ተገዷል። ከጊዜ ወደ ጊዜ እያሻቀበ ሄዶ የነበረውና በአንድ ወቅት 50 ከመቶ ደርሶ የነበረው የዕቃዋዎች ዋጋ ግሽበት አብዛኛውን ሕዝብ ክፉኛ ጎድቶታል። ሥራ አጥነት በከፍተኛ ደረጃ ተንሰራፍቷል። የወያኔ የ2014 የስታቲስቲክስ ዘገባ በከተሞች የሚገኘውን የስራ አጥ ቁጥር በአገሪቱ 17 ከመቶ በአዲስ አበባ ደግሞ 23.5 ደርሷል ብሎ ቢያስቀምጥም ቁጥሩ ከዚህ በጣም የላቀ መሆኑ ለመመስከር ጠንቋይ መሆንን አይጠይቅም። በአደንዛዥ ዕጽ ውስጥ የተሰማሩ፤ ህይወትን ለመኖር ብለው ገላቸውን የሚሸጡ ወገኖቻችን ቁጥር ለማመን በሚያስቸግር ደረጃ ላይ ደርሷል።

ትምህርት ቤቶች ተስፋፍተዋል፤ የተማሪውም ቁጥር ጨምሯል እየተባለ ብዙ ጊዜ ከበሮ ቢደለቅም የትምህርቱ ጥራት በጣም ዝቅተኛ መሆኑ ተረጋግጧል። የተባበሩት መንግስታት የሕዝብ ኑሮና ድኸነነት መለኪያ ኢትዮጵያ በጤና በኩል በጣም ዝቅተኛ ደረጃ ላይ የምትገኝ አገር መሆኗን ያጋልጣል። 75 ከመቶ የሚሆነው ሕዝባችን በተለያዩ ተላላፊ በሽታዎች የሚሰቃይ ነው። አገራችን ለ25000 ሰው አንድ ዶክተር ያለበትና ስድስት የሆስፒታል አልጋዎች አንድ ሺ ሰው የሚያስተናግድባት አገር ነች። ከጥራት ጉድለትና አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶች ከሟሟላት ጉድለት የተነሳ በአገር ውስጥ የጤና ባለሙያዎችን ለማሰልጠን ከፍተኛ ችግር ያለ መሆኑ የታወቀ ሲሆን በሙያው ሰልጥነው ከተመረቁት መካከል 70 ከመቶ የሚሆኑት በፖለቲካ ምክንያት ሆነ ተጨማሪ ክፍያ ለማግኘት ወደ ምዕራብና ሌሎች አገሮች እየተሰደዱ ይገኛሉ።

የወያኔን አስከፊና ጨቋኝ አገዛዝ በመሸሽና ከችግርና ከመከራ የተላቀቀ ህይወት ለመምራት ወደ ጎረቤት አገሮችና እንዲሁም ወደ ምዕራቡና አረብ አገሮች የተሰደደው ሕዝብ ብዛት በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠር ነው። በተለይ በወጣትነት ደረጃ ላይ ያሉ ሴት እህቶቻችን ወደ አረብ አገር ከባርነት ባልተናነሰ መንገድ እየተሸጡ ለከፍተኛ በደልና ችግር ተጋልጠው ይገኛሉ። የወያኔ ባለሥልጣናት አገናኝና አስቀጣሪ በሚል ስም የባርያ መሸጫ ንግድ ተቋማትን አቋቁመው ወገኖቻችንን በመሸጥ ከፍ ያለ ገንዘብ መዝረፍ ከጀመሩ ዓመታት አለፋቸው። እነዚህ ወገኖቻችን በአረብ አገራት ኢሰብዓዊ የሆነ በደል ደርሶባቸዋል ተደብድበው አካለ ስንኩሎች ሆነዋል፤ ተገድለዋል፤ ሀብታቸው ተበዝብዟል፤ በገፍ ታፍሰው ተባረዋል።

ሰፊው ሕዝብ ከላይ በተጠቀሰው ከፍተኛ ስቃይና ችግር በሚኖርበት ሁኔታ የወያኔ ባለሥልጣናት የኢትዮጵያን አንጡራ ሀብት በመዝረፍ ከፍተኛ ብዝበዛ እያካሄዱ ይገኛሉ። ቀደም ብሎ ኤፈርት (EFFORT) በሚል ምህጻረ ቃል በሚጠራው ድርጅት አማካይነት በተለያዩ የኢኮኖሚ መስኮች ተሰማርተው የኢትዮጵያን አንጡራ
ሲበዘብዙ መቆየታቸው የታወቀ ሲሆን ዛሬ ደግሞ ከፍተኛ ቱጃሮች በመሆን በኢንዱስትሪ፤ በውጭና አገር ውስጥ ንግድ፤ በባንክ አገልግሎት፤ በመንገድ ሥራና እንዲሁም በሌሎች አገልግሎት ሰጭ ዘርፎች ውስጥ በመሰማራት ከመንግሥት ያልተቆጠበ ድጋፍ እየተደረገላቸውና ሌሎችን ከውድድር ውጭ እያደረጉ ከፍተኛ ትርፍ በማካበት ላይ ይገኛሉ። እንደ የኢትዮጵያ አየር መንገድ፤ የቴሌኮሙኒኬሽን ድርጅት፤ የመብራት ኃይልና የመሳሰሉትን ትላልቅ ተቋማትና እንዲሁም የመከላከያ ቴክኒካል ኮርፖሬሽን እንደሚባለው ግዙፍ የሆነ የሞኖፖል ኩባንያን በመቆጣጠር ከፍተኛ ሙስናና ብዝበዛ ያካሂዳሉ።

የወያኔ ቡድን መሪዎች መሬት በመንግሥት እጅ ይሆናል የሚለውን መርህ ሲያስተጋቡ የቆዩት በመንግሥት ስም ለመዝረፍ መሆኑ ግልጽ ሲሆን ሥልጣን ከያዙም በኋላ በዚህ መስክ ያለውን ዝርፊያ አጧጡፈውታል። የወያኔ ባለሥልጣናት ሥልጣን በያዙ ሰሞን የከተማ መሬቶችን ከደኻው ላይ በመቀማት ለአባሎቻቸው አከፋፍለዋል፤ ለሀብታሞች ቸርችረው ብዙ ገንዘብ አካብተዋል። አሁንም የከተማ መሬትን ሊዝ በሚሉት የመዝረፊያ ፈሊጥ አማካይነት ከፍ ያለ ብዝበዛ እያካሄዱ መሆኑ በገሃድ የሚታይ ነው። ዛሬ በአዲስ አበባ ቁልፍ በሆነ ቦታ ላይ አንድ ካሬ መሬት በ305 000 ብር ወይም በወቅቱ የምንዛሬ ሂሳብ $15 500 ዶላር ይሸጣል። ገንዘቡን የሚቃራመቱት የወያኔ ቱባ ባለስልጣናት መሆናቸው አጠራጣሪ አይደለም።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ ወያኔ ለም የሆኑ የገጠር መሬቶችን ለውጭ አገር ከበርቴዎች በገፍ እየቸበቸበ ነዋሪዎችን ከቀያቸው እያፈናቀለና ተመጽዋች እያደረገ ይገኛል። በጋምቤላ፤ በቤኒሻንጉል ጉምዝ፤ በሱማሌ፤ በደቡብ ኦሞና በአፋር አካባቢዎች በብዙ ሚሊዮን ሄክታር የሚገመት መሬት ለውጭ ባለሃብቶች ሸጠዋል።እስካሁን ድረስ ምን ያህል ሄክታር በሊዝ እንደተሸጠ የታወቀ ነገር ባይኖርም የወያኔ ባለሥልጣናት እስከዚህ ዓመት መጨረሻ ድረስ 7.5 ሚሊዮን ሄክታር በሄክታር $2.50 ሂሳብ በሊዝ ለመቸብቸብ አቅደው ነበር። ይህን መሬት ለሀብታሞቹ ለማከራየት ከጀርባ በጉቦ ስም የሚዘረፈው ገንዘብ እንዳለ ሆኖ በግልጽ ለሊዙ ኪራይ የሚከፈለው ገንዘብ የት እንደሚገባ የሚታወቅ ነገር የለም። ተቀራምተውታል የሚለው ግምት ከእውነት የራቀ አይሆንም።

የወያኔ ባለሥልጣናት በይፋ የሚዘርፉትን የሀገር ሀብት በከፍተኛ ደረጃ ወደ ውጭ እያስወጡ መሆናቸው ከዚህ በፊት በተደጋጋሚ ተጋልጧል። የገንዘብ ግልጽነት (financial transparency) የተባለው ድርጅት ከፈረንጆቹ 2000 እስከ 2009 ባሉት ዓመታት ከኢትዮጵያ 11.7 ቢሊዮን ዶላር በሕግ ወጥ መንገድ የወጣ መሆኑን ዘግቧል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ በወያኔ ጨቋኝና በዝባዥ አገዛዝ ተማሯል። በመብት መገደብ፤ በዴሞክራሲ መጥፋት፤ በሕግ የበላይነት አለመኖር፤ በዘር ልዩነት፤ በሃይማኖትና በእምነት ጣልቃ ገብነት፤ በኑሮ ችግርና ተስፋ ማጣት፤ ...ወዘተ ያልተማረረ የኅብረተሰብ ክፍል አይገኝም። ከየትኛውም አካባቢ፤ ከየትኛውም ብሔር/ብሔረሰብ፤ ከየትኛውም የእምነት ተከታይ፤ ከየትኛውም የእድሜ ክልል የወያኔ አገዛዝን የማይጠላና እንዲወገድለት የማይፈልግ የለም።
የተጫነበትን ቀንበር ከትከሻው ለማላቀቅና የወያኔን አገዛዝ ለአንዴና ለሁሌም አስወግዶ መብቱን ለመጎናጸፍ ሕዝቡ ለበርካታ ጊዜያት ጥረት አድርጓል፤ ታግሏል፤ ቁርጠኝነቱንም በተደጋጋሚ መስዋዕትነትን በመክፈል አሳይቷል። ይሁን እንጅ የሕዝብ ኃይል ተባብሮ ባለመፈርጠሙ ጥረቱ፤ ትግሉ፤ ድካሙና መስዋዕትነቱ እስካሁን ፍሬ አላፈራም።

ለዚህም ዋናውና ዐቢዩ ምክንያት የሕዝቡን ትግል እንመራለን እናስተባብራለን የሚሉት በተቃዋሚ ጎራ የተሰለፉት የፖለቲካ ድርጅቶች የተባበረና የተጠናከረ ትግል ለማድረግ አለመቻላቸው ነው። ባለፉት 23 ዓመታት ተቃዋሚ ድርጅቶች ነን በሚሉት ጎራ ውስጥ በርካታ ለውጦች ተካሄደዋል። በአሁኑ ወቅት የወያኔን ሥርዓት አጥብቀን እንቃወማለን በማለት በብሔርና በሕብረብሔራዊ ደረጃ ተደራጅተው የሚንቀሳቀሱ የፖሊቲካ ድርጅቶች በርካታ ናቸው። ከእነዚህ ውስጥ ከፊሎች በወያኔ "ሕጋዊነት" ተሰጥቷቸው በአገር ውስጥ ይፋ የሆነ የፖለቲካ እንቅስቃሴ የሚያደርጉ ሲሆን ገሚሶች ደግሞ "ሕጋዊነት" ተነፍገው ወይም "ሕጋዊ" ሆነው መንቀሳቀሱን ሳይፈቅዱ ቀርተው በሀገር ውስጥ በህቡዕ በውጭ ደግሞ በይፋ መንቀሳቀስ የመረጡ ናቸው። ከፊሎቹ እንቅስቃሴያቸው በውጭ አገር ብቻ የተወሰነ ሲሆን ሌሎች ደግሞ በሀገር ውስጥ የትጥቅ እንቅስቃሴ እናካሂዳለን የሚሉ ናቸው።

ባለፉት ዓመታት በፖለቲካ ድርጅቶች መካከል ኅብረት ለመፍጠር ተሞክሮ በአብዛኛውን ጊዜ ሳያሳካ የቆየ ሲሆን ከብዙ ውጣ ውረድ በኋላም ተፈጥረው የነበሩ ኅብረቶች በውስጣዊ ችግርና ድክመት ፈርሰዋል። ኅብረት በፍላጎት አይመሰረትም፤ በልመናና በምለላም እውን ለማድረግ አይቻልም። መሠረታዊ ችግሮቹም እስካልተወገዱ ድረስ በአጋጣሚ እንኳ ቢፈጠር ህልውናው ሊቆይ ወይም የሕዝብን ትግል መርቶ ከግብ ሊያደርስ አይችልም። ሕዝብን ድል ሊያቀዳጅ የሚችል ኅብረት እውን ለማድረግ በመጀመሪያ የችግሩን ምንጭ ተረድቶ መፍትሔ መስጠት ያስፈላጋል።

ከተመክሮ ስንነሳ ጠንካራ የድርጅቶች ኅብረትን ለመፍጠር ወይም የተፈጠሩትን አጠናክሮ ለማስኬድ እንቅፋት ከሆኑት ምክንያቶች ውስጥ ዋናና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው። የመጀመሪያው በመጨረሻ ግብ ወይም ዓላማ ላይ የማይታረቅ ልዩነት መኖሩ ነው። የመጨረሻው ግባቸው መገንጠል የሆነ ድርጅቶችና በኢትዮጵያ አንድነት ክልል እንታገላለን የሚሉ ድርጅቶች ኃይላቸውን ሊያስተባብሩ አይችሉም። ሁለተኛው በመለስተኛ ግብ ደረጃ ልዩነት መኖሩ ነው። ወያኔ በሚያካሄድው የቧልት ምርጫ ተወዳድረን ወያኔን ማስወገድ እንችላለን ብለው በሚያምኑና ወያኔ ከሥልጣን ሊወርድ የሚችለው በሕዝብ አመጽ ወይም በጦር ብቻ ነው በሚሉት መካከል ኅብረት ለመፍጠርም ከባድ ይሆናል። ሶስተኛ በትግል ስልት ላይ ያሉ ልዩነቶች ናቸው። ወያኔ የትጥቅ ትግል ማካሄድን ወንጀለኛ አድርጎ በፈረጀበት ሁኔታ በ"ሕጋዊ" መንገድ የሚንቀሳቀሱ ድርጅቶችና "ሕጋዊነት" በተከለከሉ ድርጅቶች መካከል ይፋዊ ኅብረት ሊፈጠር አይችልም። እነዚህ ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ ሌሎችም በችግር ደረጃ ሊጠቃለሉ የሚችሉ በርካታ ጉዳዮች ይኖራሉ።

ምን መደረግ አለበት የሚለው ዐቢይና መመለስ ያለበት ጥያቄ ነው። የሚከተሉት ነጥቦች በሁሉም ወገን ትኩረት ተሰጥቷቸው ተግባራዊ ቢሆኑ ወደ ድል የሚወስደውን መንገድ ለስላሳ ከማድረጉ በተጨማሪ የትግሉን ጊዜ በማሳጠር በኩል አስተዋጽኦ ሊኖረው ይችላል እንላለን።

1. በመጀመሪያ መታወቅ ያለበት ጉዳይ በሥልጣን ላይ ያለው የወያኔ ቡድን በሰላማዊ መንገድ፤ በምርጫ፤ በባዕዳን ኃይላት ተጽእኖ፤ በልመናና በምለላ፣ ...ወዘተ ሥልጣንን የማይለቅ መሆኑ ነው። ይህ ዘረኛና አጥፊ ቡድን ከሥልጣኑ ሊወገድ የሚችለው የሥልጣኑ መሠረትና የአፈናው መሳሪያ የሆኑት የወታደሩና የጸጥታው ተቋማት በሕዝባዊ አመጽ ወይም በወታደራዊ ኃይል ሲደመሰሱ ወይም ወደ ሕዝብ ጎራ ተገድደው ሲገቡ ብቻ ነው። በተቃዋሚነት የተሰለፉት የፖለቲካ ኃይላት ይህንን ሐቅ መረዳት ይጠበቅባቸዋል። ከዚህ ውጭ ሌላ መንገድ አለ ብሎ ማለት ራስን ማታለል ወይም በጥቅምና በመሳሰሰሉት በመገዛት ሕዝብንና ወገንን ለማሞኘት መሞከር ነው።
2. ሌላ መገንዘብ የሚያስፈልገው ዐቢይ ጉዳይ የትኛውም ዓይነት የትግል ስልት መዳረሻው መሆን ያለበት የወያኔን አምባገነን አገዛዝ አከርካሪቱን መትቶና አሽመድምዶ ከሥልጣን ማስወገድ ነው። የሕዝብን ትግል እናራምዳለን የሚሉ የፖለቲካ ድርጅቶች በትግል ስልት ዙሪያ ልዩነት ሊፈጥሩ አይገባም። የትጥቅ ትግሉም ሆነ ሕዝባዊ አመጽ ከሁለቱ አንደኛው ወይም ሁለቱም ሕዝባዊ ትግሉን ለድል ሊያበቁ የሚችሉ መሆናቸው ተደጋግሞ የታየ ነው። ስለሆነም በ"ሕጋዊ" መንገድም ሆነ "ሕጋዊ" ባልሆነ መንገድ የሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ድርጅቶች በየትኛውም መንገድ ቢሆን ሕዝቡን አደራጅተው ማታገል ይጠበቅባቸዋል። በየአምስት ዓመቱ በሚደረግ የምርጫ ሆይ ሆይታ ሳይሆን በሕዝብ አመጽ ድል ይገኛል ብለው የሚያምኑና በ"ሕጋዊ" መንገድ የሚንቀሳቀሱ ድርጅቶች አመች በሆነ መንገድ (በይፋም ሆነ በሕቡዕ) ሕዝቡን አደራጅተው ትግሉን የማጠናከር ኃላፊነት አለባቸው ::
3. የፖለቲካ ድርጅቶች የአጭር ጊዜ ግብ ወያኔን ከሥልጣን አስወግዶ በሥልጣን መሰየም መሆን የለበትም። ሕዝቡ የሥልጣን ምንጭ የመሆን መብቱን ሳይጎናጸፍና ሳያረጋግጥ የሥልጣን ፍላጎት ወይም ጥያቄ መነሳት የለበትም። ሕዝብ የሥልጣን ምንጭ የመሆን መብቱ ሊረጋገጥ የሚችለው ደግሞ የመብቱ አስከባሪ የሆኑት ተቋማት ጸጥታው፤ ወታደሩ፤ ፍርድ ቤቱ፣ ...ወዘተ የግለሰብ ወይም የቡድን አገልጋዮች ሳይሆኑ የሕዝብ፤ የአገርና የሕግ ታዛዥ ሲሆኑ ብቻ ነው። የአጭሩ ጊዜ ግብ እነዚህን ወሳኝ ሥራዎች ለማከናውን መሆን ይኖርበታል። አምባገነኑ ኃይል ከሥልጣን ከተወገደ ይህን እውን ለማድረግ የሽግግር ወቅትና ጠለቅ ያለ የሕዝብ ውይይትና ስምምነትን እንዲሁም ተግባራዊ እንቅስቃሴ ማድረግን ይጠይቃል።
4. የፖለቲካ ድርጅቶች በተለይ የወያኔን "ሕጋዊነት" አግኝተው የሚንቀሳቀሱ ድርጅቶች ራሳቸውን ከወያኔ ሰርጎ-ገቦችና አፍራሾች ማጽዳትና መከላከል አለባቸው። የወያኔ ሰርጎገቦች በአመራር ላይ እንዲሰየሙና ቁልፍ ቁልፍ ቦታዎችን እንዲቆጣጠሩ እየፈቀዱ ትግል አካሂዳለሁ ማለት በሕዝብ ሕይወትና ደም መቀለድ ይመስለናል።

በአገር አንድነት፣ በብሔረሰቦች እኩልነትና በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መመሥረት ላይ ተመሳሳይ አመለካከት ያላቸው የፖለቲካ ድርጅቶች ኃይላቸውን አስተባብረው ከታገሉ የትግሉን እድሜ ለማሳጠርም ሆነ ሕዝባዊ ድልን ለመቀዳጀት እንደሚቻል ምንም ጥርጥር ሊኖር አይችልምና ይህንኑ ተግባራዊ ለማድረግ እንጣር እንላለን። ኢሕአፓ በዚህ በኩል የተቻለውን ያህል ለማድረግ ዝግጁ መሆኑን ደጋግሞ መግለጹን እያስታወሰ ሕዝብ ሁለንተናዊ መብቱን በትግሉ እስኪጎናጸፍ ድረስ የጠየቀውን መስዋዕትነት ከፍሎ ትግሉን ከመግፋት ወደኋላ እንደማይል እንደተለመደው ለሕዝብ ቃል ይገባል።

**ሕዝብ በትግሉ የሥልጣኑ ምንጭ ይሆናል!**

# ትናንትና

ካለፈዉ የቀተለ

## በቀይ ሽብር የሞት ጥላ ሥር ፤
## የጓድ ቆንጂት ተክሉ ከራሞት

### ፩

የዚሁ ልዩ ኃይል ፤

<u>ተልዕኮ</u> ፤ "ከመርካቶ አካባቢ " ሥርዓተ አልበኞችን" መመንጠር ።

<u>አካባቢያዊ ሁኔታ</u> ፤ በ "ዴሞዎች" የተወረረ የጠላት ወረዳ ሲሆን ፤ ሙሉ ለሙሉ ለማለት በሚያስችል መጠን፤ ሕዝቡ በጠቅላላ የ "ሥርዓተ አልበኞቹ" ደጋፊ ነዉ ።

<u>ስልት</u> ፤ ድንገተኛነት ባለዉ ፍጥነት ዙሪያውን በመዝጋት መርካቶን ነጥሎ መቆጣጠር ።

<u>የዕቅዱ መከወኛ ዘዴ</u> ፤ ማንኛዉንም ሰዉ ፤ እያንዳንዱን ቤት ፤ እያንዳንዱን ኪዮስክ ፤ ሠዋራ ኪስ ቦታዎችንና ማዕዘናትን ሳይቀር መፈተሽና መበርበር ። ተቀባይነት ያለዉ መታወቂያ ያልያዘን ማንኛዉንም ሰዉ ማሰር ፤ አደገኛ ተጠርጣሪዎችን በኃይል መቆጣጠር ፤ ቀይ ሽብርን ማፋፋም ።

**<u>ጊዜዉ</u> ፤ በዐዉደ ዓመቱ ሰሞን ፤ ግብይቱ እጅግ በሚደራበት የገና ዋዜማ ዕለት፤ ሐሙስ - ከጠዋቱ አራት ሰዓት ተኩል ላይ ።**

**በዚያ የተረገመ ዕለት የሰለጠኑቱ አብዮት ጥበቃዎች ፤ ተሳፍረዉ ከመጡባቸዉ ማርቼዲስ የጭነት መኪኖች ላይ እየዘለሉ በመዉረድ በየምድብ ክፍሎቻቸዉ ቦታ ቦታቸዉን ያዙ ። ጠባቂዎቹ ቀደም ብለዉ ራሳቸዉን በቅኝት ፤ በፍተሻ ፤ በእስር ፤ በሽፋንና በድርጅት መምሪያ ቡድኖች ከፋፍለዉ መድበዋል ። ለግብረ ኃይሉ ድጋፍ እንዲሰጡ የተመደቡ ወታደሮችና ፖሊሶችም ምድብ ሥፍራዎቻቸዉን ያዙ ።**

የጥቃቱ ዒላማ የሆነዉ ጠላትስ ምን ይመስል ነበር ? ይህን በሚመለከት ፤ ጥቂት ምስለ ሃሳቦችን አቀርባለሁ ። መርካቶን በጥቂት ቃላት አጠቃልዬ ልስለዉ ብሞክር ፤ ማለት የምችለዉ እጅጉን የሚያደነጋግር ጉራንጉር መሆኑን ነው -- የአስፋልት ፤ የአፈር ጥርጊያ መንገድ ፤ ዉሽቅሽቅ ያሉ ቤቶች ጫካ ። ከሰዎች አንስቶ እስከ ቆሌዎቻቸዉና ሥምሪቶቻቸዉ ፤ ብሎም እስከ ሥነ ህንጻ ድረስ ሁሉ ነገር ድብልቅልቅ የሚሉበት ፤ ቅጣምባሩን ባጣ መልኩ ትዉፊታዊዉ ከዘመናዊዉ ፤ አሮጌዉ ከአዲሱ ጋር በአንድ የሚገማሸሩበት ሥፍራ ነዉ ። መርካቶ ሁለ ነገሩ በአያዎ (የማይመስል ግን እዉነት የሆነ ) የተመላ ነዉ። ከአንዲት በዉድ ልብሶች ከተሽቀረቀረች እመቤት ጎን ለጎን ያልጠገገና የሚያዥ ቁስል የወረሰዉን አካሉን ገሚስ ርቃን የተወ የሥጋ ደዌ በሽተኛ የሚታይበትን ያህል ፤ በአቧራማዉ ጎዳናዉ ላይ ሽንጠ ረዥሙ ማርቼዲስ ቤንዝ መኪና ከአቅም በላይ ተጭኖ ከሚያቃስት አህያ ጋር ይጋፋበታል ። የሚያስደንቀዉን ያህል ሲረዱት አዳጋች የሆነዉ መርካቶ ለተቃዋሚ ፖለቲከኞች ብቻ ሳይሆን ራሳቸዉን ከፖሊስ ለሚደብቁ ዜጎች ሁሉ መሰወሪያ ሆነዉ የሚያገለግሉ በርካታ ቤቶች ይገኙበታል ።

እርግጥ ነዉ ፤ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) በጠቅላላዉ ሕዝብ ልብና አዕምሮ ዉስጥ ዘልቋል ። ይሁን እንጂ ከድርጅቱ አንጻር መርካቶ ልዩና ሁነኛ ግምት የተሰጠዉ አካባቢ ነዉ ። መርካቶ ለእኛ ፤ አልጄሪያዉያን በጸረ ቅኝ አገዛዙ የትግል ዘመን "ካዝባህ " ብለዉ ለሚጠሩት ሥፍራ ይሰጡት የነበረዉን ያህል ልዩ ግምት ያላት ናት ። በመላዉ ዓለም ከሚገኘዉና አስከፊ በሆነ ጭቆናና ድህነት ከሚማቅቀዉ ሕዝብ ዉስጥ የተወሰነዉ ክፍል መርካቶ ዉስጥ ይኖራል ። ከዚህም በላይ መርካቶ የቱጃር ነጋዴዎች ፤ የመሃከለኛና የዝቅተኛ ቸርቻሪዎች ፤ የደላሎች ፤ የሊስትሮዎች ፤የሴትኛ አዳሪዎች ፤የቡና ቤትና የመሸታ ቤቶች ባለቤቶች ፤ የሠራተኞች ፤ የተማሪዎች ፤ የለማኞች ፤ ለአጭር ወይም ለረዢም ጊዜ ጉብኝት ወደ ሀገሪቱ መዲና የመጡ ገጠሬዎች ፤ የጡረተኛ ፖሊሶችና ወታደሮች ፤ በተለያየ ደረጃና አይነታ የሚገኙ ቁጭበሉዎች ፤ የስዉር ንግድ አካሃጆች ፤አነስተኛ ደመወዝ የሚከፈላቸዉ ሠራተኞች ፤ ወዘተ....ሁሉ መኖሪያ ናት ። ከነዚህ ዉስጥ አብዛኛዎቹ የኛዉ ዐይኖችና ጆሮዎች ሲሆኑ ለወታደራዊዉ አገዛዝ የነበረንን የከረረ ጥላቻም ይጋሩናል ።

ትንንሾቹ ሊስትሮዎች ቃፊሮቻችን የነበሩ ሲሆኑ መርካቶ ዉስጥ ከሚተረማመሰዉ የሰዉ መዓት ዉስጥ አንድን የደኅንነት አባል በቀላሉ ነጥሎ የማዉጣቱን ጥበብ ተክነዉበታል ። የቡና ቤት ባለቤቶች ፤ በተለይም የየምሽቱ ተረኛ ሴቶች ፤ ተዝቆ ለማያልቀዉ መረጃ ምንጮቻችን ነበሩ ። ከአፈር መደቦቻቸዉ ላይ ተቀምጠዉ አትክልት ፤በከፊል የተበላሹ ፍራፍሬዎች ፤ ቆሎና ቅመማ ቅመም የሚሸጡት የጉሊት ነጋዴ ሴቶችም ንቁ ደጋፊዎቻችን ናቸዉ ። እነዚህ የጉሊት ቸርቻሪዎች በቅርጫቶች ቁልል ተከብበዉ ፤ በመደዳ የቁጢጥ ከተቀመጡበት ሆነዉ ከፍ ባለ ድምጽ ሲንጫጩ ለተመለከተ በዙሪያ ገባቸዉ የሚከናወነዉን ድርጊያ የሚያስተዉሉ አይመስለዉም ። ለእኛ ግን ንቁ የመረጃ አቀባዮቻችን ነበሩ ። ካሉበት ሆነዉ የደኅንነት ሠራተኞችን ወይም ለተልዕኮ የተሰማራዉን አሳሽ ቡድን በቀላሉ ነጥለዉ ከለዩ በኋላ ብዙዉን ጊዜ እኛ -ታጋዮቹ የተለመደዉን "የቁም ስብሰባ" ወደምናደርግበት ጥጋት በጥድፊያ በመምጣት እንድንበተን ያስጠነቅቁናል ። በወቅቱ አብሮን መገኘት የሌለበትን መሳሪያ ወይም የሚበተን ወረቀት ይዘን ከሆነም በፍጥነት ተቀብለዉ ይደብቁልናል ። እዚያዉ በዚያዉ የሚያቀናብሯቸዉ የብልግና ስድድቦችና አካላዊ ምልክቶች የሚታከሉባቸዉ የጦፉ የጸብ ትዕይንቶች የአሳሹን ቡድን ትኩረት በማስለወጥ ወይም እንቅስቃሴዉን በማዘግዬት ያግዙናል ።

የእነዚህ ሴቶች ምልከታ እጅግ የሰላ መሆኑ ፤ የተለመደዉን " የዝንብ ጠንጋራ አዉቃለሁ ፤" የጉራ አባባል ለእዉነት ያቀርበዋል ። የአገዛዙን የደኅንነት ሠራተኞች ለይተዉ የሚያዉቋቸዉን ያህል እኛንም (ራሳችንን ለመለወጥ የምንጠቀምባቸዉ ዘዴዎች ሳያግዷቸዉ ) በቀላሉ ይለዩን ነበር ። በተቻለኝ አቅም አንዲት ምስኪን የቤት ሠራተኛ ተመስዬ በወጣሁባቸዉ ጊዜያት በአጠገባቸዉ ሳልፍ በስሜ ጠርተዉ አንድ ወይም ሁለት ሙዝ በነጻ ይሰጡኝና ሀዘኔታ በተጫነዉ ዐይን እያዩ "አይዞሽ፤" እያሉ ያበረታቱኛል ። ( ይታያችሁ ፤ በጊዜዉ ንግድ ፤ በስሙኒ ስድስት የገዙትን ሙዝ ቸርችረዉ ሰላሣ ሳንቲም ብቻ ነበር የሚያጣሩት ።)

ስለእነዚያ ሴቶች ማሰቡ በራሱ ህቡዕ ስለነበረዉ የሕይወቴ አንጓ እንድጽፍ በአንክሮ ይጎተጉተኛል ። ስለ ተመክሮዬ ስናገር ከሌሎች የተለየ ላይሆን እንደሚችል አበክሬ ማሳወቅ እወድዳለሁ ። በሺዎች የሚቆጠሩት ጓዶቻችን እጅጉን የገዘፈና የተለያየ የህቡዕ ትግል ተሞክሮ ያላቸዉ ናቸዉ ። በመሆኑም ከገዛ ራሴ ተመክሮ ብቻ በመነሳት በህቡዕ የተኖረዉ ሕይወት ይህንን ወይም ያንን ይመስላል ከሚል ማጠቃለያ ለመድረስ ያስቸግረኛል ። የኔዉ ታሪክ ፤ ብዙዎቹ ጓዶች ከኖሩት አንደኛዉና ተዳባይም የመሆኑን ያህል በራሱ ምልዐት ያለዉ ተሞክሮ ነዉ ።

### ፪

እንደ አንድ "ሕጋዊ" ሰዉ ሳደርጋቸዉ የነበሩትን እንቅስቃሴዎች በመግታት ራሴን ለመደበቅ የተገደድኩት በ፩፱፻፷፰ ዓ.ም አጋማሽ ላይ ነበር ። ባለትዳር ወጣቶች አስጠግተዉኝ የተጠለልኩባት ባለአንድ ክፍሏ ወሻቃ ቤት አዲስ አበባ ከተማ ዉስጥ ግንፍሌ አካባቢ ትገኛለች ። ቤቲቱ ፤ የባልና ሚስቱን መኝታ ፤ ተዳብሏቸዉ ይኖር የነበረ አንድ ሌላ ሰዉ ታጣፊ የመንገድ አልጋ ፤ እንዲሁም የምግብና የወጥ ቤት ዕቃዎች ማስቀመጫ የሆነዉን አንድ ጠረጴዛ አፋፍጋ ይዛለች ። ስንጥቅጥቅ የበዛባቸው የቤቱ የጭቃ ምርግ ግድግዳዎች በከፊል በሲኒማ ማስታወቂያ ወረቀቶች ተለጣጥፈዋል ። (ከእነዚሁም አንዱ "ቫላቺ ፔፐርስ" በሚል ርዕስ የሚታወቀዉ ፊልም ማስታወቂያ እንደነበር አስታዉሳለሁ ።) ቤቷ ለአራት ሰዎች የማትበቃ፤ በዉስጧም ርስበርስ ሳይገጫጩ ለመተላለፍ የማታስችል ነች ። የዕድል ሆኖ ግን በደባልነት የሚኖረዉ አራተኛዉ ሰዉዬ ሥራዉ በዋናዉ የንግድ ባንክ የሌት ዘበኛነት ነዉ ። የቤቱ አባ ወራ በአንድ የግል ት/ቤት የሚያስተምር በመሆኑ ቀን ቀን እቤት አይዉልም ። የቤት እመቤቲቱ ደግሞ የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪ ብትሆንም በወቅቱ የሠርክ በነበረዉ የተማሪዎች ረብሻና የትምህርት ማቆም አድማ ሳቢያ ት/ቤቷ በመዘጋቱ የተነሳ ቤት ነበር የምትዉለዉ ። በደባልነት ተጠግቶ የሚኖረዉን ሰዉ ግን እንኳን እኔ እዳባዮቹም አያዉቁትም ። ከአንድ ጣሪያ ሥር ለመኖር ያስገደዳቸዉ በጊዜዉ የነበረዉ ከፍተኛ የመኖሪያ ቤት እጥረት ነዉ ።

መኖሪያ ሠፈራችንም ራሱ ጭንቅንቅ ያለ ነዉ ። የኛ መኖሪያ ከሆነዉ ክፍል ጋር ከተያያዘዉ ሌላ ቤት ጋር አንድ ባለ አርባ ሻማ የኮረንቲ መብራት በጋራ እንጠቀማለን ። ለነገሩ እንጂ በዚያ ሠፈር ዉስጥ ከጎረቤቶቻችን ጋር የምንጋራዉ መገልገያ ኮረንቲዉ ብቻ አልነበረም ። በወል የምንቀዳዉ ቧምቧ ሁሌም ስለሚያፈስስ ፤ ዙሪያውን በቦካዉ ጭቃ ላይ ተረማምዶ ዉኃ ለማግኘት ከላስቲክ የተሠራ ቦት መጫማት ያስፈልግ ነበር ። ከጋራ አገልግሎት መስጫዎቻችን ሁሉ ዝነኛዉ በሠፈሩ ማዕከላዊ ሥፍራ ላይ የሚገኘዉ የመጸዳጃ ቤት ሲሆን ከመወጣጫ ደረጃዎቹ ግርጌ ከምር የሚያስቁ ትዕይንቶች በየዕለቱ ይከናወኑበታል ።

አንዳንዶቹ ፤ ለምንም ነገር ደንታ ሳይኖራቸዉ ገብተዉ ለሰዓታት ያህል ይወዘፉበታል ። ሌሎቹ ደግሞ ፤ በተለይም ሴቶቹ ፤ ወደ መጸዳጃዉ ቤት ሲገቡና ሲወጡ እንዲታዩ ፈጽሞ አይፈልጉም ። (ሴቶች ይህ ስነ-ሕይወታዊ ግዳጅ አይመለከታቸዉም በሚል ቅድመ እሳቤ የተነሳ ይሆንን ?? ) ፤ እናም ሴቶች ሽንት ለመከፈል ወደ መጸዳጃ ቤቱ የሚያመሩት በድብቅ ፤ በፊቶቻቸዉ ገጽታ ላይ ከፍተኛ ሀፍረት እየተነበበ ሲሆን ፤ ግራና ቀኝ ተገለማምጠዉ ማንም እንደማያያቸዉ ካጣሩ በኋላ እንደ ጥይት ተተኩሰዉ ይገባሉ። አንዳንዶች ደግሞ ከተፈጥሮአዊዉ ድርጊት ጋር የተቆራኙ አሳፋሪ ድምጾችን ለመሸፈን ሲሉ መጸዳጃ ቤት ዉስጥ ሆነዉ ይዘፍናሉ ወይም ያፏጫሉ ።

ለግምት ከሚያስቸግር በላይ እጅግ ከሚገማዉ ከዚያ የመጸዳጃ ቤት ዘልቀዉ ሲገቡ ፤ የኮምፔስታቶ ወለልና ከወለሉ አምስት ሳንቲ ሜትር ያህል ከፍ ባሉ አራት ቀጫጭን ጣዉላዎች ዙሪያዉን የተለበጠ የጉድጓዱ ጠባብ አፍ ፤ እንዲሁም ሰዎች የተጠቀሙባቸዉን የጽዳት ወረቀቶችና የጋዜጣ ቁርጥራጮችን የያዘዉ የቆሻሻ መጣያ ቅርጫት ይታያሉ ። ጉድጓዱ ላይ የተገጠመ አንዳችም መቀመጫ የሌለ በመሆኑ ተገልጋዩ ሰዉ የቁጢጥ በመቀመጥ ዐይነ ምድሩን አስተካክሎ ወደጉድጓዱ ማስገባት ይጠበቅበታል ። በዚያ ረገድ ፤ ከመጸዳጃ ቤቱ ተጠቃሚዎች ብዙዎቹ የተዋጣላቸዉ አልነበሩምና የነበረዉን ሁኔታ መገመቱ ላንባቢያኑ አይገድድም ። መጀመሪያ ላይ የቁጢጥ መቀመጡ ጡንቻ የሚሸመቅቅ ህመም እያስከተለብኝ ተቸግሬ የነበረ ቢሆንም ዉዬ አድሬ ልላመደዉ በቅቻለሁ ።

መላመድን የጠየቀኝ ሌላዉ ጉዳይ ምግብን ይመለከታል ። የምንመገበዉ ምግብ ሁልጊዜም የማያጠግብና ጣዕም የለሽ ነበር ። ሻይና ቡናማ ቀድሞ ነገር አይታሰቡም ። በወቅቱ ስኳር በቀበሌዎች አማካይነት የሚታደል ሲሆን ቡና ደግሞ በኪሎ ሃያ ብር ገብቷል ። ሁለት ሰዎችን ብቻ በያዘና በመምህር ደመወዝ በሚተዳደር ቤት ዉስጥ ከሚታየዉ የኑሮ ሁኔታ በመነሳት በላብ አደሮች ፤ በዘበኞችና በሌሎቹ ዝቅተኛ ገቢ በነበራቸዉ ቤተሰቦች መኖሪያ ሊኖር የሚችለዉን ሁኔታ መገመቱ ያን ያህል አላዳገተኝም ። አጋጣሚዉ በህይወቴ ለመጀመሪያ ጊዜ ከእዉነተኛዉ ረሃብ ጋር አስተዋዉቆኛል ። ከዚያ በፊት ከረሃብ ጋር የነበረኝ ዕዉቂያ ትርፍ የሰዉነቴን ክብደት ለመቀነስ ምግቤን በምቆጣጠርበት ጊዜ ብቻ የተከሰተ ነበር ። በዚህም ሳቢያ እርስ በራሱ የሚቃረን ስሜት አደረብኝ ። በአንድ በኩል ፤ አሳዛኝና አስቸጋሪ የሆነዉን ህይወት ለሚገፉትና ፤ በማይሟላ ፍላጎትና በእጦት መሃከል የዉጥር ለተያዙ ወገኖች ሁሉ ሀዘን ገባኝ ፤ ባዶነትም ተሰማኝ ። በሌላ በኩል ደግሞ ፤ ከልቤ ከማስብላቸዉና ከምጨነቅላቸዉ ዝቅተኛ የኅብረተሰቡ ክፍሎች የአኗኗር ዘይቤ ጋር ራሴን ለማዋሃድ ዕድል ባገኘሁበት በዚያ አጋጣሚ እጅግ ደስ ተሰኘሁ ።በጥቅሉ ፤ አጋጣሚዉን መፈተኛዬም ፤ የኑሮ ጉስቁልና በዕዉኑ ምን እንደሆነ እንድማርበትም የተሰጠኝ ልዩ ዕድል አድርጌ ነበር ያየሁት ።

ለሽፋን በተጠቀምኩበት በአዲሱ ማንነቴ ፤ ከባሌ ጋር ተፋትቼ ከምኖርባትና በወለጋ ጠቅላይ ግዛት ከምትገኝ ትንሽዬ ከተማ ወደ አዲስ አበባ የመጣሁ የመምህሩ አስጠጊዬ እህት ነኝ ። ከቤቱ እንድኖር ያስጠጋኝ ሰዉ በአጋጣሚ የሚናገረዉ አማርኛ ደግሞ በጣሙን የኦሮሚኛ የአነጋገር ስልት የተጫነዉ ሲሆን እኔ ግን በተቃራኒዉ ከፈለቅሁበት ማኅበረሰባዊ ዳራ የተነሳ ተመሳስዬ መገኘቱ አልሆነልኝም ። በጊዜዉ የተጠቀምኩበት አማርኛዬ ዳር አገር ከሚገኝ የገጠር ከተማ ከመጣች አንዲት አርሶ አደር ሴት ይልቅ ለአንድ የሰላም ጓድ አባል (አሜሪካዊ) አነጋገር ይበልጥ የሚቀርብ ነበር ። ሆኖም ግን ፤ ሲያድለኝ ያ የተጠጋሁበት ሰዉ ፤ አንድም - በፖለቲካዉ ረገድ ዐይኑን ገና ያልገለጠ ፤ አንድም ደግሞ - ደክሞት ከሥራዉ ወደቤቱ የሚገባ ነበርና ነገሮችን አገጣጥሞ ለመመልከትና በመስቀልኛ ጥያቄ ሊያጣድፈኝ የሚያስችለዉ በቂ ጊዜ አልነበረዉም ።

**ይቀጥላል........**

# ከሃይሉ ገሞራው ግጥሞች የተቃረሙ

## ከበረከተ መርገም ለቅምሻ

"ከጥንት ጀምሮ ስናየው የኖርነው
ሲነድ ሲቃጠል የሚስቅ እሳት ነው"

" በኔነቴ ክልል እናንተን አይቼ የናንተን ስናገር፣
ላለመኖር መኖር፣ ለመኖርም መኖር፣
ላለመማር መማር፣ ለመማርም መማር፣
ለማግኘት መታገል፤ ለማጣትም መጣር፣
ለማትረፍ መዋተት ለመክሰርም መጋር
ላለማሰብ ማሰብ፣ ለማሰብም ማሰብ፣ የኋላ ኋላ ግን
እንደኳስ ለመንጠር፣
ላለማወቅ ማወቅ፣ ለማውቅም አውቆ፣ በጥበብ ደርጅቶ
በሀብታት ለመኖር፣
ይህ ነው ፍልስምናው፣ የዘመኑ ነገር፣ የጊዜያችን ታምር፣
ሆኖብኛል ለኔ፣ ዕውር፣ እንቆቅልሽ የሰዎች አኗኗር።"

እንደዚህ ከሆነ፣ የተፈጥሮህ ጠባይ
ለስሜት ከሆነ፤ የመኖርህ ጉዳይ
ችግርን ተደሰት፤ ደስታን ተሠቃይ።"

ሆኖም ያዳሜ ልጅ ብትሰማኝ ተመከር
የዳዋ ውስጥ አይጥ የሜዳው ጓጉንቸር
የቆንጥር ከርከሮ፤ የደኑ ውስጥ አነር
የመንደር ድምር ሕዝብ የበረሃው ነብር
የጉድጓዱ አሸን፣ የባሕሩ ውስጥ አዞ፣ የረግረጉ
እልቂት፣ የኩይሳው ቁጫጭ፣ ያየር ጀፎ አሞራ
ከቶ ሁሉም ነገር፤
በደመ ነፍስ ኃይል የሚንቀሳቀሰው ጠቅላላውም ፍጡር
አኸኮ አመንዠጉ፣ ከርትሶ ደቁሶ፣ አድቆ ሰልቆ፣ ስልቅጦህ
እንዳትቀር፣
አስብ ተመራመር፣ ጠንቁል ተፈላሰፍ፣ አጥብቀህ
ተራቀቅ፣
ላንተነትህ ስትል ሁኔታው ቢረቅም
በዘመኑ ነገር
ይህ ነው የገፋፋኝ ዛሬ ለመናገር...."

ያሰብከው ዓላማ አልሆን ብሎ ሲከሸፍ
ሁኔታው ሲጠጥር፣
ጠጣሩ እንዲላላ፤ የላላውን ወጥር ...."

////////////////////////////////////////////////////////////

## መከረኛዋ እማማ ኢትዮጵያ

"ቸንክሮ የያዘሽ ካስማዉና አዉታሩ
ዓይነቱ ብዙ ነዉ ባድባሩ ባዉጋሩ
ከቶ እንዴት እናርጊሽ ልንፈታሽ ከሥሩ"

////////////////////////////////////////////////////////////

## የማዳም ቀበቶ

ትዝ ይለኛል ቤቴ የተወለድኩበት፣
ትዝ ይለኛል ቀየው ድሮ ያደግሁበት
አዎን ትዝ ይለኛል ያኔ የኖርኩበት።
የጠጣሁበቱ ወንዙ ኩሬው ባሕሩ
ያጋጥሁበት ሥርዶ ሜዳው ሸንተረሩ
የማመስኳበት የግርግም ድንበሩ
ተኝቼ እማድርበት ጋጣው ፍጉ ሣሩ፣
ትዝታዬኪ ነው ውል የሚለኝ ብጠፋም ካገሩ።

ምንም እንኳ ዛሬ ተለይቶኝ ሕይወት
በድን ጠፍር ሆኜ ብዙም ነገር ብስት
ሁሉም ትዝ ይለኛል ሕያው ሆኜ ሳለሁ ድሮ የሠራሁት
አዎ በጥጃነት አዎ በምቦሳነት፣ በወይፈኑ ሆነ ኋላም በኮርማነት
በመጨረሻም ላይ በሠንጋ በሬነት
ትዝ ይለኛል ሁሉም ድሮ የሠራሁት።
በተፈጥሮም ይሁን ወይም በሌላ ኃይል
ተንከራተት ብሎኝ በዘር ማንዘር ዕድል
ወጥቼ ካገሬ
በሞት ተባርሬ
ፓሪስ አገኛለሁ፤ በፓሪስ ነኝ ዛሬ
የማዳምን ወገብ አሽሜ ጠፍሬ።
ፓሪስ እምብርቷ ላይ ስኖር ቆይቻለሁ
በማዳም ወገብ ላይ በመውጣት በመውረድ
ስቃዬና አያለሁ።

////////////////////////////////////////////////////////////

## ክንፍማ ቢኖረኝ

"ክንፍ የለሽ ሆኜ እንጅ፣ ክንፍማ ቢኖረኝ
መች ያስችለኝ ነበር ፤ እኔ አንቺን ሳልጎበኝ ?
መች ያስችለኝ ነበር፣ እስከ ዛሬ ድረስ፣
ያችን ውብ ሀገሬን፣ ሳላይና ሳልደርስ!
ከምድር ጥጋት ሆኖ፣ ያለሁበት ጋጣ፣
ርቀት ድል መታኝ፣ ስታገል ልመጣ!
ተቸግሬ እንጅ ነው፣ ሉንጎው እግሬ ቢያጥር፣
አለያማ በርግጥ፣ እጎበኝሽ ነበር።
አንደ ወፍቹማ ኖሮኝ ቢሆን ያ ክንፍ!
ባልዘገየሁ ነበር፣ እዚህ ስንከረፈፍ!
በርሬ አያት ነበር ፣ ምን ዚቅ እንደዋጣት
ጉስቁሏን ሀገሬን፣ እርግብግቧን እናት!
ተባራሪ ውሬ ከሚያላግጥብኝ
ከንፌ አያት ነበር፣ ክንፍማ ቢኖረኝ!!
እረ አዕዋፋት፣ ክንፋችሁን ልዋስ፣
ሀገሬን አይቼ ደርሼ እስከመለስ።
ንቧንማ ሆኜ ብገባ ከሀገር!
የናቴን ተባዮች በጠዘጠዝኩ ነበር!"

////////////////////////////////////////////////////////////

## እሳት ጠፉ ይበል

"ምንኛ ደደብ ነው ፍፁም ልበ- ድፍን
ድርግም አለ የሚል በድፍረት እሳትን ።
ይዳፈናል እንጅ መች ይጠፋል እሳት
መፋፋም ቅራኔው፣ ገንፍሎ እስኪወጣ
በዚያች የሐቅ ዕለት።
በግለት ፈንድቶ ከተዳፈነበት ሲወጣ አደባባይ፣
ያንዕለት ይሆናል ከጭድ ጋር ጋብቻው ፣
ሃይሎጋ የሚያሳይ።
ይሰጣል አይቀርም ትክክለኛ ፍርድ
ለዚያ አባይ ሁሉ ወደመ እያለ ላለ ሲያወናበድ!
ይሰጣል አይቀርም የፍትህ ብያኔ
ሲፎክር ለኖረው፣ የለም ባካቢ እያለ ሲያቅራራ፣
ኃይለኛ ያለኔ።
ይዳፈናል እንጅ ከቶ መች ይጠፋል፤
ውስጥ ውስጡን ተብላልቶ አጅሬ ያ እሳት፤
መጫጫሱ ሲግል፣
ቅራኔው ሲያገሳ በቅጽበት ይነሳል፣ ደግሞም ያቃጥላል።
ያንቀላፋል እንጅ ከቶ መች ይሞታል፣
በደጋፊዎቹ የእምነት አባባል
በማይለወጠው የአጋሮቹ ቃል፤
በዳግም ትንሳኤው ለድል ቀን ይነቃል።
ያሸልባል እንጅ በዱር መኻታው ቤት፤
ችግኞች እስካሉ መች ይጠፋል እሳት!

## ገሞራው

ከመስፍን ጉግል

እድለኛስ ነበረ ፣ ገሞራው ሲፈጠር፤
በኪነ ጥበቡ ፣ ተንቆጥቁጦ ሊኖር፤
እሱ ግን ጀግና ነው ፣ ስጦታውን ንቆ፤
አሳልፎ ሰጠ ፣ ሕይወቱን አውልቆ፤
አንዴ ሳይኖራትም ፣ በፈቃዱ ገሎ፤
ለተገፋው ጭቁን ፣ ለወገኑ ብሎ፡፡
እንጂማ ቢል ኖሮ ፣ መጀመሪያ ራሴን፤
የምን ደሞ አገር ፣ ልጡር ደግ እናቴን፤
ለዚህ ያበቃኝን ፣ ምስኪኑን አባቴን፤...
ትምህርቱ ላይ ተግቶ ፣ ዲግሪውን ተሸክሞ፤
ማዕረግ በያይነቱ ፣ አጊጦ ተሸልሞ፤
''ከመኳንቱ'' ጋር ፣ ሚኒስትር ተሹሞ፤
ንጉሱን አወድሶ ፣ ጎንበስ ለጥ ብሎ፤
ዶክተር ፕሮፌሰር ፣ ኖቤል ተቀብሎ፤
ሁልቆ መሳፍርቱን ፣ ''ገሞራው!...'' አስብሎ፤
መኖር ይችል ነበር ፣ በሀብት ተከልሎ፡፡
ግና...የሱ ማንነት ፣ ምድቡ ከትላልቆቹ፤
ገድሉና ታሪኩ ፣ ከሊቃውንቶቹ፤
ከመሲህዎቹ ጋር ፣ እንደሐዋርያቱ፤
ሆነ እጣ ፈንታው ፣ መከራን ማየቱ፤
ለእውነት ዘብ መቆም ፣ ለሌሎች መሞቱ፤
ቀድሞ እንዳለፉት ፣ እንደ ሰማእታቱ፡፡
በቡረቃው ዘመን ፣ በጎረምሳነቱ፤
ልጅ ያቦካው ለራት ፣ በሚተረትበቱ፤
ያ አይከሰሴውን ፣ የአጼውን ስርዓት፤
በድፍረት ሲታገል ፣ ለሀገሩ አርነት፤...
ዕራቡንም ሳይቀር ፣ ብቸኛ ሀያሉን፤...
ወያኔን ሲያርደው ፣ በብዕር አለንጋው፤
ተገንጣይን ሲያወግዝ ፣ ከሀቅ ሲያጋጨው፤
ባንዶች ሲያዋርዱት ፣ ካገር ሲያሳድዱት፤
ባእዳንም ሲያግቱት ፣ አውቀው ሲያሳብዱት፤
ብቻውን ስቃዩን ፣ እንደተጋተረ፤
መንፈሰ ጠንካራ ፣ አርአያ ነበረ፡፡
ለኢትዮጵያ ፍቅሩ ፣ እንዲህ ሲብከነከን፤
ሲነድም ሲቃጠል ፣ ይህ ሁላ ዘመኑን፤
የሕዝቡ ሰቆቃ ፣ ነፍሱን ሲያስጨንቀው፤
ስደቱ ረሀቡ ፣ እረፍት ሲነሳው፤
ሲታመም ሲቃትት ፣ ሲሞተው... ሲሞተው...
እንደሻማ ቀልጦ ፣ ሳያርፍ አረፈ፤
ከእውነት ጋር ጸንቶ ፣ በእውነት አለፈ፡፡
ይብላኝ ለባእዳኖች ፣ ሀፍረት ለባንዳዎች፤
እሱ አንደው ተከቷል ፣ አዕላፍ ገሞራዎች፤
ያ ትውልድ ያለፈው ፣ ዛሬም በትግል ያለው፤
የሐዋርያው ፍሬ ፣ የባለቅኔው ዘር ነው፤
ገሞራው አይሞትም ፣ በነሱ ሕያው ነው፡፡
አገር ነጻ ሲሆን ፣ ወደፊት በትግል፤
ባንዳ ቦታ ሲለቅ ፣ ታሪክ ሲስተካከል፤
ጠቢብ የሚገባው ፣ ትውልድ ይመጣል፣
የዛኔ ገሞራው ፣ አክሊል ይቀዳጃል፡፡

*በሳምንት ሁለት ጊዜ -ረቡዕና እሁድ- የሚተላለፉትን የፍኖተ ዴሞክራሲን ፕሮግራሞች www. Finote.org ያዳምጡ;። በየሳምንቱ ቅዳሜ በ2፡00 PM የሚተላለፈውን የፍኖተ ኀብረ የኢሕአፓ ድምፅ ፕሮግራም እንዲሁም በ www. Finote.org ድረ ገጽ ማግኘት የሚቻል ሲሆን በተጨማሪ በቀጥታም ሆነ በማንኛቸውም ጊዜ 401-347-0175 በመደወል ማዳመጥ ይቻላል።*

## ገና አልተዋወቅንም!!

ከዘነበ በቀለ

ያገር አፈር ይቅመስ፣ ብለው የሚሉት ቧልት፣
ከየት የመጣ ነው?!ይኸን መሳይ ቅዠት!
ቆይቶ የለም ወይ?!የሀገሩን አፈር፣ ሀይሉ ከቀመሰ፣
ለጋምቤላው ብሎ፣ ለአፋሩ ብሎ፣ ለአማራው ብሎ፣
ለኦሮሞው ብሎ፣ እንዲያው በጠቅላላው ለኢትዮጵያ ሀገሩ፣
ያልተናገረበት የትኛው ዘመን ነው?
የትኛው ዘመን ነው?!ተይዞ በፍርሃት
ሀይሉ ደሃ ከድቶ?!ፀጥ ለጥ ያለበት?!
መቼ ነው ገሞራው?!የወያኔን ደባ ያላጋለጠበት?!
ጭራቅ ብሎ ስሎ፣ ያላወገዘበት?!
የትኛው ዘመን ነው?!ወገኔን አትንኩ ብሎ ያላለበት?!
ላገዛዝ አልመች፣ ብሎ ያላመፀበት?
ኖሯል ታዲያ! ሀይሉ በነዚህ ዘመኑ!
ቀርቶለት ነበረ፣ በየሶስት ወሩ፣ በፖሊስ በአለቃ ታስሮ መመርመሩ?
የትኛው ዘመን ነው፣ አፈር ያልቀመሰበት?
የትኛው ዘመን ነው፣ ሞቶ ያልተነሳበት።
ከትውልድ ለይቶ፣ ለማኖር ደብቆ?
ስራዎቹን ሰርቆ፣ ለመቅበር አርቆ፣
ማሰቡ ማለሙ፣ ተጠቦ ተጨንቆ፣
ሀይሉ አገር ካልገባ፣ ዕቅ እንቅ መባሉ!
ውክልና ለማግኘት፣ እንዲያ መሽከርከሩ!
እውን ወዳጅነት ነው -በማሰብ ለሃይሉ?
ሀይሉማ!ገሞራው፣ ከደሀው ጋር ደሃ -ሆኖ ያልተገኘበት፣
አንደበት ላጣው ህዝብ አንደበቱ ሆኖ ያልተናገረበት፣
ምንም ዘመን የለም፣ ህዝቡ ሲጨፈጨፍ፣ ወጣቱ ሲታረድ ተቀምጦ ያየበት፣
እናም ሀይሉ ኖሮ!ኖሮ!ኖሮ ሞተ -ከመባሉ፣
ሲሞት ሲሞት ኖሮ፣ ሞተ ለትንሳኤ –ይሻላል ብሂሉ!
መጥፋት ብሎ መኖር እንዳለው እራሱ፣
በየመጣጥፉ በብዕር ድግሱ።
ስለዚህ ጎበዝ ሳታመሀኝ ብላኝ ብሏል ከያኒው፣
አመካኝቶ መብላት ስለሰለቸው።
ንግድ የምትነግዱ፣ ባለኮንዶምኒየሞች፣
የልማት ህልመኞች፣ አልሙ በራሳችሁ፣
የምን ጠጋ ጠጋ፣ ሀይሉን መሻታችሁ?!
ከብት ባልዋለበት፣ ኩበት ለምትለቅሙ፣
ምንም ችግር የለም፣ እርስ በርስ ነውና እርስ በርስ ተግማሙ።
ግና! ለናንተ ሲዝ!በተሸጠ መሬት አስከሬኑ እንዲያርፍ ምክንያት የሆናችሁ፣
አትጠራጠሩ!አይቀርም የጃችሁ!



50 South Pickett Street Suite 214
Alexandria, VA 22304

# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)
# Ethiopian People´s Revolutionary Party (EPRP)

ህዳር 2 ቀን 2007 ዓ.ም.

## በዝነኛው ኃይሉ ገብረ ዮሐንስ (ገሞራው) ዜና እረፍት የተነሳ ከ ኢሕአፓ የተሰጠ መግለጫ

እውቁ ገጣሚ፥ ታላቁ ደራሲና ግዙፉ የሀገራችን ቅርስ ለረጅም ዓመታት በስደት መከራውን ሲያይ በቆየበት በስቶክሆልም (ስዊድን) ከተማ በዚህ ሰሞን አርፏል። ታዋቂዋንና አቻ የሌላትን በረከተ መርገምንና በርካታ ሊሎች የግጥም መድበሎችንና ድርሰቶችን ያቀረበው ኃይሉ በቤተ ክህነት ትምህርት የላቀ ዕውቀት የነበረው፤ የቅኔም አባት ሆኖ የቆየ ታላቅ የአገር ቅርስ ነበር ።

ኃይሉ ለዘመናዊው ትምህርት ወደ ዩኒቨርስቲ ከገባ ጀምሮ በተራማጅ አስተሳሰብን ያንጸባርቅ በነበረው የተማሪ እንቅስቃሴ ግንባር ቀደም ሆኖ ሲታገል ከሌሎች ስምንት ተማሪዎች ጋር ከዩኒቨርስቲ ተባሮ እንደነበር ይታወቃል ። ገሞራው በአጼው ዘመን ሲታገል በተደጋጋሚ ለበርካታ ጊዜዎች ተይዞ ታስሮ የነበረ ሲሆን ጨካኝ በሆኑ የጸጥታ ሰራተኞች ድብደባና ስቃይን ተቀብሏል ። ገሞራው ለሰፊውና ጭቁን ሕዝብ አለኝታ ሆኖ ገና ከወጣትነት ዕድሜው ጀምሮ የታገለ ጀግና ነበር ። ለኢሕአፓ ደግሞ የማይታክት ደጋፊና ወዳጅ ሆኖ የቆየ በመሆኑ ኢሕአፓ በዚህ ታላቅ ሰው ዕረፍት የተሰማው ሀዘን ትልቅ ነው። ቢሆንም ገሞራውን በስራውና በቅርሱ ለማክበርና አርአያነቱንም ለማስተጋባት እንጥራለን እንጂ እሱ ራሱ በማይፈልገው መንገድ ራስ ልንደፋና ልንሽማቀቅ−−ልንበሳጭ አንችልም ።
"ዛሬ ቢያወሩልኝ አልሰማም የሻገተ ወሬ የቀመለ
ድፍን አበሻ ቢቀላምድ እንዲህ እንዲህ እያለ
ገዳሙን ትቶ ኮበለለ
ይህ አባ ቆቡን ጣለ
ብሎ የጻፈውንም ግጥም በአንክሮ የምናስታውሰው ሲሆን በተለይም በረከተ መርገም የዚያን ጊዘውን ወጣት ትውልድ የቃኘና ያነሳሳ ታሪካዊ ግጥም መሆኑንም የምንዘነጋው አይደለም ። ገሞራው "ያሰብከው ዓላማ አልሆን ብሎ ሲከሽፍ/ሁናቴው ሲጠጥር/ጠጣሩ እንዲላላ የላላውን ወጥር" ብሎ የቋጠረው መልዕክት እስከዛሬም ወቅታዊ ሆኖ ቅኝትና ግንዛቤ ሰጪ ሆኗል ።

ኃይሉ ገብረ ዮሐንስ ወደ ቻይና ለከፍተኛ ትምህርት ሄዶ በዚያም ብዙ መከራን ችሎ የቆየ ሲሆን ከዚያ ሲለቅም ከ400 ገጾች በላይ የሆነ የቻይንኛ (ሀን) የእንግሊዝኛ የፈሊጣዊ አባባሎች መጽሃፍን ጽፎ አሰራጭቷል ። ገሞራው ከማረፉ በፊት የስራው ስብስቦች በቅጾች ደረጃ ይታታሙ ዘንድ ለኢሕአፓ

ሰጥቶ በዚህም መሰረት ለህትመቱ ሀገር ወዳዶች ጭምር መዋጮ ለግሰው የህትመቱ ስራ በሂደት ላይ ይገኛል ። ገሞራው በስደት ወደ ኖርዌይና ስዊድን በመጣበት ወቅትም በነዚህ ሀገሮች ያሉ ወያኔዎችና ሻዕቢያዎች ፍዳ ያሳዩት ሲሆን ለወያኔዎችና ሻዕቢያዎች ተንኮል ግንባሩን ሳያጥፍ፤ ቃል ኪዳኑን ሳይሽር ችግሮቹን ተቋቁሞ ሲታገል ቆይቷል ። ይህን የኢትዮጵያ ታላቅ ቅርስ የሆነውን ውድ ዜጋ ለመታደምና ለመንከባከብ ከፈተኛ ርብርቦሽና ጥረት መደረገ የነበረበት ቢሆንም በዜጎች ችላ ተብሎ የከፋ ችግርና ስቃይ የደረሰበት መሆኑንም ሳንጠቅስ ብናልፍ ጉድለት ይሆናል ። ገሞራው ውሾ (ወያኔ ወ ሻዕቢያ ላይ) የኢትዮጵያ ሕዝብ ድልን እንደሚቀዳጅ ሙሉ እምነት የነበረው ሲሆን ለወያኔ ድለላና ግብዣም ጆሮ አልሰጥ በማለቱ መከራው ተባብሶበት ቆይቷል ። ገሞራው የኢሕአፓ ባለውለታ ነው−− የኢትዮጵያ ሕዝብ ጀግናና ጽኑ ልጅም ነው ። በወያኔው እንደተገደለው ወዳጁ ጻጋዬ ደብተራውም ፍርሓት አልባ፤ ጽኑና ታላቅ የኪነት ሰውም የነበረ ነውና በማረፉ ሀገራችን ትጎዳለች ። የተወው የጀግንነት ቅርስ ግን ወጣቱን ትውልድ ለትግል ይቃኛልና ገሞራው ሁሌም አብሮን ነው፤ ሁሌም ለጸረ ኢትዮጵያ ሃይሎች ሁሉ አንቀጥቃጭ ሆኖ የሚቆይም ነው ።

ኢሕአፓ ለገሞራው ቤተሰቦችና ወዳጆች ሁሉ ጽናቱን ይስጣችሁ ይላል።
የገሞራው ቅርስና አርአያነት ትግላችንን ያጅባል፤ ያጠናክራል ።

EPRP
P.O.BOX 73337
Washington DC, 20056
USA

EPRP
BP 30022
92276 Bois Colombes cedex
France

Email ESPIC@aol.com
Website WWW.EPRP.com
Tel. 202 291 4217 Fax: 202 291 7645